ለ) ማናቸውም ከዚህ ወጪ የሚደረግ ክፍያ ሲሆን የሚከፈለው ሰው ክፍያውን ለማግኘት የሚገባው መሆኑን፤

፪· ቢሮው በዚህ አንቀጽ መሠረት ሊሟላ የሚገባውን የማረጋገጥና የማጣራት አፈጻጸም ሥርዓት ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል ።

፳፯· <u>በበጀት ዓመት መጨረሻ የሚሰጥ የችሮታ ጊዜ</u>

እያንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት የበጀት ዓመቱ ከማለቁ በፊት ለቀረበለት የክፍያ ጥያቄ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በ፴ ቀናት ውስጥ፤

ሀ) የበጀት ዓመቱ ከማለቁ በፊት ለታዘዙና ለተረከባቸው ዕቃዎች

ለ) የበጀት ዓመቱ ከማለቁ በፊት ለታዘዙና ለተሰጡ አገልግሎቶች እና

ሐ) የበጀት ዓመቱ ከማለቁ በፊት ማናቸውም የክፍያው ጊዜ የደረሰ ወይም በውል በተገባው ግዴታ መሠረት መከፈል ያለበትን መዋጮ ወይም ሌላ ተመሣሣይ ግዴታ መከፈል አለበት፤

፳፰· <u>የካፒታል በጀት የሚታይበት ልዩ ሁኔታ</u>

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፳፯ የተመለከተው ቢኖርም ፤ የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት ክፍያውን ያፀደቀው ከሆነ የካፒታል ወጪ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በ፴ ቀናት ውስጥ ሊፈጸም ይችላል ።

<u>ክፍል ስድስት</u>
<u>ሥራ ላይ ያልዋለው በጀት አስተዳደር</u>

፳፱· *<u>ሥራ ላይ ያልላወለ በጀት</u>*

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፯ እና ፳፰ የተመለከቱት እንደዚሁም ቢሮው ስለጉዳዩ የሚያወጣው መመሪያ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፤ ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደ እና ወጪ ሳይደረግ ወይም ሥራ ላይ ሳይውል የቀረ ሂሣብ ሁሉ ሥራ ላይ መዋሉ ቀርቶ ለቢሮው የትሬዠሪ ፈሰስ ይደረጋል ።

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም የዕርዳታና የብድር ሂሣብ በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ሥራ ላይ መዋሉ ሊቀጥል ይችላል ።

፴· <u>የቅድሚያ ክፍያ</u>

በተሰጠበት የበጀት ዓመት መጨረሻ ያልተመለሰ ፤ ያልተወራረደ ወይም ያልተተካ ማናቸውም የቅድሚያ ክፍያ ሂሣብ በዓመቱ ከሚቀርበው የመንግሥት ሂሣብ ጋር ተጠቃሎ ሪፖርት መደረግ አለበት ።

፴፩· <u>ስለማቻቻል</u>

ማናቸውም የቅድሚያ ክፍያ ሂሣብ በእንዲህ ያለውን ክፍያ በሚያዘው ደንብበ መሠረት በሙሉ ወይም በከፊል ያልተከፈለ ፤ ያልተወራረደ ወይም ያልተመለሰ ሲሆን፤

ሀ) ከጡረታ አበል በስተቀር የቅድሚያ ክፍያውን ለወሰደው ሰው በክልሉ መንግሥት ከሚከፈል ማናቸውም ገንዘብ ፤

ለ) የቅድሚያ ክፍያውን የወሰደው ሰው ሞቶ እንደሆነ ከጡረታ አበል በስተቀር ለወራሾቹ ከክልሉ መንግሥት ከሚከፈል ማናቸውም ገንዘብ ላይ ተቀናሽ ሊደረግ ይችላል ።

(b) Where the payment is to be made in any other situation, that the payee is entitled to the payments.

2. The Office may issue directives to put into effect the execution procedures of certification and verification that are prerequisits in accordance with this Article.

27. Grace Period Given at the End of Fiscal Year

Each public office shall, for payment requests rendered before the end of the fiscal year, effect payment within the 30 days following the end of the fiscal year:

(a) for goods ordered and received prior to the completion of the fiscal year,

(b) for services ordered and received prior to the completion of the fiscal year, and

(c) for any contribution or other similar obligation whose time of payment is due or which payment shall be made according to the obligation entered in the agreement prior to the completion of the fiscal year.

28. *Exception for Capital Budget*

Notwithstnding the abovementioned Article 27, where the Regional Executive Committee has approved payment prior to the completion of the fiscal year, capital expenditure may be effected within 30 days following the end of the fiscal year.

PART SIX
Management of Unspent Funds

29. *Unspent Funds*

1. With out prejudice to the abovementioned Articles 27 and 28 of this Proclamation and directives issued by the Office with this regard, all funds approved for the fiscal year but which were not spent or appropriated shall lapse and be credited back to the Treasury Account of the Office.

2. Notwithstanding sub-Article (1) of this Article, funds of grants and loans shall be retained in the consolidated fund and may continue to be appropriated where necessary.

30. *Advances*

Every advance fund that is not credited back, accounted for or exchanged by the end of the fiscal year in which it was allocated shall be reported together in the public accounts prepared for the year.

31. *Sef-off*

Every advance fund that is not, wholly or partially, paid, accounted for or credited back in accordance with Regulations governing such payments, may be deducted from:

(a) any fund, except pensions, payable by the Regional Government to the person who procured the advance payment;

(b) any fund except pensions, payable by the Regional Government to the heirs of the person who procured the advance payment, where the person is deceased.

፴፪. *የወጪ ተመላሽ*

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የክልሉ መንግሥት የተቀበለው ማናቸውም ፤

፩. የወጪ ተመላሽ ፤

፪. የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ ፤

፫. በብልጫ የተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ ፤

፬. በተመላሽ ሂሣብ ፤ በተመላሽ ታክስ ወይም ላይ ክፍያ ላይ የዋጋ ማስተካከያ በመደረጉ ምክንያት የሚገኝ ተመላሽ ጭምር ፤

፭. የጉዳት ካሣ በመክፈሉ ምክንያት የተገኘ ገንዘብ ወይም፤

፮. በመንግሥት መ/ቤት ሀብት ላይ የደረሰው ጉዳት ወይም ኪሣራ እንዲተካ በቀረበ ጥያቄ ምክንያት የሚገኝ ገንዘብ ፤ ቀደም ሲል ለዚሁ ጉዳዩ የተደረገው ወጪ ወይም የቅድሚያ ክፍያ ሂሣብ በተያዘበት የበጀት ርዕስ ሥር ገቢ ሆኖ መመዝገብ አለበት ።

ክፍል ሰባት
የክልሉ መንግሥት ዕዳ

፴፫. *የመበደር ሥልጣን*

የፌዴራል መንግሥት የሚወሰነው የብድር ገደብ እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭ ፤ ፴፮ እና ፴፯ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ የክልሉ ምክር ቤት ካልፈቀደ በስተቀር በክልሉ መንግሥት ወይም በክልሉ መንግሥት ስም ገንዘብ ለመበደር ወይም ዋስትና ለመስጠት አይቻልም ።

፴፬. *ገንዘብ የማሰባሰብ ሥልጣን*

፩. የክልሉ መንግሥት ወይም በክልሉ መንግሥት ስም ገንዘብ ለማሰባሰብ ሥልጣን ሲሰጥ ፤ ገንዘቡን ለማሰ ባሰብ በሚፈቅደው አዋጅ የተመለከተው እንደተ ጠበቀ ሆኖ ፤ የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በዚሁ አዋጅ መሠረት ገንዘቡ በሙሉ ወይም በከፊል በቀጥታ ብድር ፤ ወይም በዋስትና ሠነድ አማካኝነት እንዲሰ ባሰብ ሊፈቅድ ይችላል ።

፪. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተውን ለማከ ናወን እንዲችል የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የቢሮው ኃላፊ ወይም እርሱ የሚወክለው ሌላ የቢሮው ባለሥልጣን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እንዲፈጽም ሥልጣን ይሰጠዋል ።

ሀ) ሠነዱ የሚወጣበትንና ዕዳው ተከፋይ የሚሆን በትን ቀን እና የዕዳውን አከፋፈልና የወለዱን መጠን ለመወሰን ፤

ለ) የዋስትና ሠነዶችን እንዳስፈላጊነቱ ለመሸጥ ፤

ሐ) የቀጥታ ብድር ወይም የዋስትና ሠነዶችን ማውጣትና መሸጥን በሚመለከት ስምምነት ለመፈጸም ፤ እንደገና ለመደራደር ፤

መ) በቢሮው ኃላፊ ተቀባይነት ባላቸው የውል ቃሎችና ሁኔታዎች የብድሩን ገንዘብ በከፊል ወይም በሙሉ መልሶ ለማበደር ፤

፴፭. *ቀጥታ ብድሮችን ወይም የዋስትና ሠነዶችን ለመክፈል ስለሚወሰድ ብድር*

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የክፍያው ጊዜ የደረሰ ወይም ተመላሽ እንዲደረግ ጥያቄ የቀረበበትን የቀጥታ ብድር ፤ ወይም የዋስትና ሠነድ ክፍያ ለመፈጸም የሚያስችል ገንዘብ መበደር እንዲችል ለቢሮው ኃላፊ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

፴፮. *ለተጠቃለለው ፈንድ አስተዳደር ስለሚወሰድ ብድር*

የክልሉ ሥራአስፈጻሚ ኮሚቴ የተጠቃለለውን የመንግ ሥትተ ፈንድ በበቂ ሁኔታ ለማስተዳደር የሚያስችል ገንዘብ እንዲበደር ለቢሮው ኃላፊ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል ።

32. *Refunds of Expenditure*

Any amount received by the Regional Government within the fiscal years as:

1. refund of expenditure,
2. refund of advance payments,
3. refund of money overpaid,
4. a rebate, tax rebate or extra money received due to adjustments made on price,
5. money obtained due to indemnification, or
6. money obtained due to a claim instituted for the restitution of damages or expenses incurred on the property of a public office shall be registered as paid under the budget heading which relates to the expense or advance payment previously made for this purpose.

PART SEVEN
Debt of the Regional Government

33. *Authority to Borrow*

Without prejudice to the limits set by the Federal Government and to Articles 35, 36 and 37 of this Proclamation, no money shall be borrowed or securities issued by the Regional Government or in the name of the Regional Government unless and otherwise authorized by the Regional Council.

34. *Power to Raise Money*

1. Where power is granted to raise money by the Regional Government or in the name of the Regional Government, subject to the proclamation that authorizes the raising of the money, the Regional Executive Commitee may, persuant to this proclamation, allow the raising of the money, wholly or partially, through direct loans or securities.
2. With a view to enabling the implementation of sub-Article (1) of this Article, the Regional Executive Commitee may grant power to the Head of the Office or to the authority designated by him to the effect of executing the following:
   (a) determine the date of issuance and maturity of bonds and the manner of payment and rate of interest,
   (b) sell of securities as may be necessary,
   (c) conclude and re-negotiate agreements with respect to the issuance and sale of direct loans and securities.
   (d) on-lend all or a portion of a loan, subject to the terms and conditions acceptable to the head of the Office.

35. *Loans Taken to Redeem Direct Loans or Securities*

Without prejudice to Article 36, the Regional Executive Committee may, upon the maturity of the time of payment or the presentation of a request of payment for a direct loan or securities, grant the head of the Office with the power to borrow such money that enables redemption.

36. *Loans Taken for the Management of Consolidated Fund*

The Regional Executive Committee may grant the head of the Office with power to borrow money that enables the proper administration of the Consolidated Public Fund.

፴፯. *ጊዜያዊ ብድሮች*

የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሕግ የተፈቀዱትን ክፍያዎች ለመሸፈን የተጠቃለለው ፈንድ በቂ መስሎ ሳይታየው ሲቀር ፤ የተጠቃለለው ፈንድ ለክፍያዎቹ ሊበቃ ይችላል ብሎ ከሚያምንበት የገንዘብ መጠን የማይበልጥና ከስድስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ተመልሶ የሚከፈል ገንዘብ እንዲበደር ለቢሮው ኃላፊ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል ፡፡

፴፰. *የዕዳ ገደብ*

በሌላ አግባብ ባለው አዋጅ የተደነገገ ገደብ ሳይቃረን ፤ የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በቀጥታ በመበደርም ሆነ ዋስትና በመስጠት የክልሉ መንግሥት ከአገር ውስጥ ሊበደር የሚችለውን ዕዳ መጠን ይወስናል፡፡

፴፱. *የብድር ግዴታዎች ክፍያ*

በክልሉ መንግሥት ወይም በክልሉ መንግሥት ስም የተወሰዱ ቀጥታ ብድሮች ፤ እና የዋስትና ሰነዶች ዋና ገንዘብ፤ በዚሁ ላይ የሚከፈል ወለድ እና የአስተዳደር ወጪ ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ የሚታሰብ ሆነው ከዚሁ ወጪ ተደርገው ይከፈላሉ ፡፡

፵. *ኪሣራ*

የቢሮው ኃላፊ ፡—

፩. የዋስትና ሠነዶቹን የመግዣ ዋጋ በሙሉ ወይም በከፊል ከፍለው ዋስትናው ወይም የከፈሉበት ገንዘብ ያልተመለሰላቸው በመሆኑ በገንዘብ ከፋዮቹ ላይ የደረሰውን ማናቸውም ኪሣራ ፤ እና
፪. የዋስትና ሠነዱን ለማስመለስ በማናቸውም ሰው ላይ የደረሰውን ኪሣራ ፤ ከተጠቃለለው ፈንድ ወጪ አድርጎ ሊከፍል ይችላል፡፡

፵፩. *ዋስትና*

፩. የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከሚያወጣው ደንብ ጋር የማይቃረን እስከ ሆነ ድረስ የክልሉ መንግሥት ለግዴታ መፈጸም ዋስትና ሊሰጥ ይችላል ፡፡
፪. ዋስትናን በሚመለከት የሚደረግ ክፍያ ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ወጪ ተደርጎ ይከፈላል ፡፡

፵፪. *የመንግሥት ዕዳ አስተዳደር*

የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የክልሉን መንግሥት ዕዳ ስለ ማስተዳደር ፤ በዚሁ ዕዳ ላይ ወላድ ስለሚከፈልበት ሁኔታ እንዲሁም ለዋስትና አስተዳደር አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል ፡፡

፵፫. *የክልል መንግሥት ዕዳ ስለማስተላለፍ*

፩. የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የክልሉ መንግሥት ዕዳ ስለሚተላለፍበት ሁኔታ ደንብ ሊያወጣ ይችላል ፡፡
፪. የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሦስተኛ ወገኖች ዕዳን ለክልሉ መንግሥት ሊያስተላልፉ ስለሚችሉበት ሁኔታ ደንብ ሊያወጣ ይችላል ፡፡
፫. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ዕዳ ሊተላለፍ አይችልም ፡፡

፵፬. *የመንግሥት ዕዳ ስለመመዝገብ*

ቢሮው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በሚመለከት የተሟሉና ዝርዝር የሆኑ መዛግብት ይይዛል ፡፡

፩. በክልሉ ምክር ቤት በተሰጠ ፈቃድ ቀጥታ ብድሮችን እና የዋስትና ሠነዶችን በማውጣትና በመሸጥ ብድር የተወሰደበትን ገንዘብ ፤

37. *Temporary Loans*

Where it appears to the Regional Executive Committee that the Consolidated Fund is not sufficient to cover the legally authorized disbursements, it may grant the head of the Office with the power to borrow an amount of money not exceeding that necessary to ensure the Consolidated Fund to be sufficient for payments and for a repayment period not exceeding six months.

38. *Debit Limits*

The Regional Executive Committee shall, without being contrary to limitations set under other relevant proclamations, determine the debit limits that the Regional Government may borrow locally either through direct loans or the rendering of securities.

39. *Payment of Loan Obligations*

The principal of money obtained by the Regional Government or in the name of the Regional Government through direct loans or securities, and interest and administrtive expenses incurred on them shall be paid and be accounted from the Consolidated Fund.

40. *Losses*

The head of the Office may make payment out of the Consolidated Fund:

1. for any cases sustained by subscribers of securities who have paid all or part of the purchase price of the securities and who have not received back the securities or the amount of money they paid; and,
2. for losses sustained by any person in the redemption of the securities.

41. *Sureties*

1. Without prejudice to the Regulations issued by the Regional Executive Committee, the Regional Government may issue sureties for the performance of an obligation.
2. Payments made in respect of a surety shall be paid out of the Consolidated Fund.

42. *Management of Public Debts*

The Regional Executive Committee may issue Regulations that are necessary for the management of the debt of the Regional Government, the payment of interest thereon and the administration of sureties.

43. *Assignment of Debt of The Regional Government*

1. The Regional Executive Committee may issue Regulations with respect to the assignment of debts of the Regional Government.
2. The Regional Executive Committee may issue Regulations with respect to the manner of assignment of the debts of third parties to the Regional Government.
3. No debt shall be assigned unless and otherwise pursuant to sub-Articles (1) and (2) of this Article.

44. *Regulation of Public Debt*

The Office shall keep a complete and detailed record in respect of the following:

1. money obtained as loans through the issuance and sale of direct loans and securities authorized by the Regional Council,

፪· በዚህ ዓይነት በብድር የተገኘው ገንዘብ መግለጫ ፤
፫· በብድር የተገኘውን ገንዘብ በሚመለከት የተከፈለ ዋና ገንዘብ እና ወለድ ፤
፬· ቀጥታ ብድሮች ፤ እና ዋስትና ሠነዶችን ከማውጣት ፤ ከማስተዳደር እና ከመክፈል ጋር በተያያዘ ለሚሰጡ አስተዳደራዊ አገልግሎቶች እንዲሁም ዋስትናዎችን መስጠትን ፤ ማስተዳደርና መክፈልን በሚመለከት ለተደረጉ አስተዳደራዊ አገልግሎቶች ለሬጂስራሮች ፤ ለፊናንስ ወኪሎች እና ለሌሎች የተከፈለውን ገንዘብ መጠን ፤
፭· ዋስትናዎችን በሚመለከት የተፈቀዱበትን ፤ ስለዋስ ትናው መግለጫ ፤ የተከፈለውን መጠንና ጠቅላላ የአስተዳደር ወጪዎች ፤

ክፍል ስምንት
የመንግሥት ገንዘብ ኢንቨስት የማድረግ ሥልጣን

፵፭· የተረፈ ፈንድ ኢንቨስትመንት

የቢሮው ኃላፊ በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ የሚገኘው ገንዘብ ለጊዜው ለክፍያ የማይፈለግ ሲሆን ፤ ይህንን ገንዘብ የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚያወጣው ደንብ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ፤ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተገቢ ናቸው በሚላቸው የዋስትና ሰነዶች ላይ ኢንቨስትመንት ሊያደርግ ይችላል ።

፵፮· የጥሪት ፈንድ ማቋቋምና ማስተዳደር

፩· የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የጥሪት ፈንድ የሚቋቋ ምበትንና የሚተዳደርበትን ሁኔታ ይወስናል ።
፪· ለጥሪት ፈንድ የሚያስፈልገው ገንዘብ ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ወጪ ሆኖ ይከፈላል ።

ክፍል ዘጠኝ
የክልሉ መንግሥት ንብረት

፵፯· ስለመያዝና ስለማስወገድ

በሌሎች አዋጆች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ካልሆነ በስተቀር የክልሉን መንግሥት ንብረት መያዝ ወይም ማስወገድ አይቻልም።

፵፰· የንብረት ጥበቃና ቁጥጥር መዛግብት

እያንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ቢሮው ስለንብረት ጥበቃና ቁጥጥር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በመ/ቤቱ ኃላፊነት ሥር የሚገኘውን የመንግሥት ንብረት በሚመለከት ብቃት ያለው መዝገብ መያዝ አለበት።

ክፍል አሥር
የመንግሥት ሂሳብ

፵፱· የሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ

ቢሮው የእያንዳንዱን የበጀት ዓመት የሒሣብ ሪፖርት በማዘጋጀት በተቻለ ፍጥነት ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል።

፶· የሪፖርቱ ይዘት

የመንግሥት ሂሣብ ሪፖርት የሚቀርበው ቢሮው በሚያ ወጣው መመሪያ መሠረት ሆኖ የሚከተሉትን ያካትታል።

፩· የሂሣብ መግለጫዎች
ሀ) የበጀት ዓመቱ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች፤
ለ) የክልሉን መንግሥት የበጀት ዓመቱ ገቢዎችና ወጪዎች፤

2. declaretion of loan money obtained as such,
3. the principal and interest paid with respect to money obtained as loans,
4. the amount of money paid to registers, fiscal agents and others in connection with administrative services rendered for the issuance, management and payment of direct loans and securities; and for administrative services made in respect to the issuance, management and payment of securities,
5. with respect of securities their authorization, a declaration of the security, the amount paid and administrative expenses.

PART EIGHT
Authority to Invest Funds

45. *Investment of Surplus Fund*

Where the money found in the Consolidated Fund is not immediately required for payment, the head of the Office may, subject to Regulations issued by the Regional Executive Committee, invest on securities which are declared as appropriate by the Regional Executive Committee.

46. *Establishment and Management of Sinking Fund*

1. The Regional Executive Committee shall provide the manner of establishment and management of sinking funds.
2. Money required for sinking funds shall be paid out of the Consolidated Fund.

PART NINE
PROPERTY OF THE REGIONAL GOVERNMENT

47. *Acquisition and Disposition*

Without prejudice to other proclamations, the property of the Regional Government shall not be acquired or disposed of unless and otherwise pursuant to Regulations issued by the Regional Executive Committee.

48. *Record for Custody and Control*

The executive head of each public office shall, subject to the directives issued by the Office for the custody and control of property, keep an efficient record with regard to public property falling under the domain of the office concerned.

PART TEN
PUBLIC ACCOUNTS

49. *Preparation and Submission of of Reports*

The Office shall prepare a report of accounts for each fiscal year and shall submit to the Regional Council as soon as possible.

50. *Collect of the Report*

The public accounts report shall be submitted in accordance with the directives issued by the Office and shall contain the following.

1. Financial Statements
   (a) the financial transactions of the fiscal year,
   (b) the revenues and expenditures of the Regional Government for the fiscal year,

ሐ· የተጠቃለለው ፈንድ

መ. የክልሉን መንግሥት ዕዳዎች፤ ዋስትና የተገባባ ቸውና የሚጠበቁ ግዴታዎች፤

ሠ· ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደው፤ ወጪ የተደረገውን እና ወጪ ያልተደረገውን የገንዘብ መጠን፤

ረ· የዘቀጠ ፈንድ ካለ ይህንኑ

ሰ· የክልሉን መንግሥት የበጀት ዓመቱን የፋናንስ እንቅስቃሴዎች እና አቋም የሚያሣዩ ሌሎች ሂሣቦችና መረጃዎች፤

፪· የክልል ኦዲት ጽ/ቤት የክልሉን መንግሥት የፋናንስ መግለጫ መርምሮ የሰጠውን አስተያየት፤

፫· አግባብነቱ በቢሮው የታመነበት ሌላ ተመሣሣይ መረጃ፤

፶፩· *የገንዘብ ዓይነት*

የክልሉ መንግሥት ሂሣብ የሚያዘውና ሪፖርት የሚደረገው ኢትዮጵያ ብር ይሆናል።

፶፪· *መዛግብት*

፩· የያንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት ኃላፊ ቢሮው በሚያ ወጣው መመሪያ መሠረት የመ/ቤቱን ኃላፊነት የሚመ ለከቱ የፋናንስ መዝገቦችን ይይዛል፤ ለቢሮውም ያቀርባል።

፪· እያንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት የበጀት ዓመቱ ከተጠ ናቀቀ በኋላ በተቻለ ፍጥነት ሂሣቡን ዘግቶ ለቢሮው ሪፖርት ያቀርባል።

ክፍል አስራ አንድ
ግዢና ውሎች

፶፫· *ውሎች ስለሚገዙባቸው ደንቦች*

የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስለውሎችና ክፍያ አፈጻጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል። ይህም ደንብ ስለግዥና ስለውሎች አፈጻጸም ለውሎች ስለሚሰጠው ዋስትና እና የውሉን አፈጻጸም ማስከበሪያ የሚሆኑ ድንጋጌዎችን የሚያካትት ሊሆን ይችላል።

፶፬· *የውል ግዴታ*

፩· ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደ በጀት መኖሩን ሳያረጋግጥ የክልሉ መንግሥት የሚገደድበት ውል መፈፀም የለበትም።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም አፈፃፀሙ ከአንድ የበጀት ዓመት በላይ ለሚወስድ ፕሮጀክት የረዥም ጊዜ ውል ለመዋዋል ለፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ዓመት የተፈቀደ በጀት መኖሩን ማረጋገጥ ብቻ በቂ ይሆናል።

፶፭· *የግዥ አፈጻጸም*

የማናቸውም ዕቃና አገልግሎት ግዢ የሚፈጸም ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል። ይህም መመሪያ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ስለሚገዙበትና ግዢው ለሕዝብ ግልጽ ስለሚደረግበት ሁኔታ ዝርዝር መረጃዎችን የሚይዝ መሆን አለበት።

፶፮· *የግዥ ደንቦችን ወቅታዊነት ስለማረጋገጥ*

ቢሮው ከክልሉ መንግሥት ግዢና ውሎች ጋር የተያያዙ የአስተዳደር ፖሊሲዎችንና ደንቦች በየጊዜው መውጣታቸ ውንና በሰፊው መሠራጨታቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

(c) the Consolidated Fund,

(d) debts, guaranteed debts and contingen liabilities of the Regional Governmen

(e) the amount of money appropriated, expended and unexpended in the fiscal year,

(f) sinking funds, if any, and

(g) such other accounts and information tha show the financial transactions and positio of the Regional government in the fiscal year

2. The opinion given by the Regional Audit Offic after examining the financial statement of th Regional Government.

3. Other related information deemed appropriate b the office.

51. *Kind of Currency*

The accounts of the Regional Government shall be maintained and reported in Ethiopia birr.

52. *Records*

1. The head of each public office shall, pursuant to the directives issued by the office, keep and provide to the Office the financial records with regard to the public body of which he is responsible.

2. Each public office shall, at the end of the fiscal year, close its accounts and provide a report to the Office as soon as possible.

PART ELEVEN
Procurement and Contracts

53. Regulations of contractors

The Regional Executive Committee may issue Regulations concerning contracts and the execution of payment. The Regulatons may include provisions with respect to procurement and the peformance of contracts, securities provided for contracts and sureties for the contracts and sureties for the performance of the contract.

54. Contractual Obligations

1. The head of any public office shall not conclude a contract which obliges the Regional Government unless he has ascertained the availability of funds appropriated for the fiscal year.

2. Notwithstanding sub-Article (1) of this Article the ascertaining of the availability of a budget appropriation in the first year of a project shall be sufficient to conclude a long-term contract where the execution of the project requires more than one fiscal year.

55. Regulation of Procurements

The procurement of any goods and services shall be executed pursuant to the directives issued by the Office. The directives shall contain detailed information with respect to the manner of procurement of goods and services and as to how the procurement is disclosed to the public.

56. Review of Procurement Regulations

The Office has the responsibility of ascertaining that administrative policies and regulaitons which are related with procurements and contracts of the Regional Government are being regularly issued and exhausitively disseminated.

ክፍል አሥራ ሁለት
የፌዴራላዊ መንግሥትና የክልሉ መንግሥት የፋይናንስ ግንኙነቶች

፶፯· ጠቅላላ

፩· በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥትና በክልሉ መንግሥት መካከል የሚኖረው የፋይናንስ ግንኙነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ለክልሉ የሚሰጠውን ዓመታዊ የበጀት ድጋፍ ይጨምራል።

፪· የክልሉ መንግሥት ከፌዴራላዊ መንግሥት የሚቀበለውን የበጀት ድጋፍ ድጎማ በሚመለከት በፌዴራሉ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት ሂሣቡን ይይዛል። ለፌዴራሉ መንግሥት ሪፖርት ያቀርባል።

፶፰· የአገር ውስጥ ብድር

፩· የፌዴራሉ መንግሥት ክልሉ ሊበደር የሚችለውን የገንዘብ መጠን መወሰን እንዲችል የክልሉ መንግሥት ለፌዴራሉ መንግሥት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሁሉ መስጠት አለበት።

፪· የክልሉ መንግሥት የሚወስደው ብድር የተገኘው ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ውጪ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውንም በብድር ከተገኙ ገንዘብ ላይ የሚፈፀም ክፍያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚያስተዳድረው ይሆናል።

፫· የክልሉ መንግሥት የሚወስደው ብድር ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ውጪ የተገኘ ሲሆን፣ የክልሉ መንግሥትና የፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ሚኒስቴር በጋራ የሚስማሙበት የአስተዳደር ሥርዓት ተፈፃሚ ይሆናል።

፶፱· የውጭ ምንዛሪ

ቢሮው የክልሉ መንግሥት የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት በሚመለከት ለፌዴራሉ መንግሥት የገንዘብ ሚኒስቴር ተገቢውን መረጃ መስጠት አለበት።

ክፍል አሥራ ሦስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፷· መመሪያዎች

ቢሮው ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፷፩· ስለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መጥፋት

የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከቢሮው የሚያገኘውን አስተያየት መሠረት በማድረግ በሚከተሉት ላይ ደንቦች ሊያወጣ ይችላል።

ሀ) በማናቸውም መንገድ የመንግሥት ገንዘብ ወይም ንብረት ሲጠፋ መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች

ለ) የጠፋው የመንግሥት ገንዘብ ከተፈቀደው በጀት ላይ ስለሚቀነስበት ሁኔታ፣

ሐ) ከዚህ በላይ በፊደል ሀ የተመለከተው ማናቸውም የጠፋ የመንግሥት ንብረት ወይም ገንዘብ በመንግሥት ሂሣብ ውስጥ ሪፖርት የሚደረግበትን ሁኔታና ስለሚመዘገብበት መንገድ፣

፷፪· ጥፋቶችና ቅጣቶች

፩· የመንግሥት ገንዘብ ለመሰብሰብ፣ ለማስተዳደር ወይም ክፍያ ለመፈጸም በማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት የተቀጠረ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ተሿሚ፣

ሀ) በሕግ መሠረት ሊከፈለው ከሚገባ በቀር የተመደበበትን ሥራ በማከናወኑ ማናቸውንም ክፍያ ከተቀበለ፣

ለ) የክልሉን መንግሥት ገንዘብ በማጭበርበር ወይም ሌላ ሰው እንዲያጭበረብር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተባበረ ወይም ያሴረ፣

PART TWELVE
Financial Relations of the Federal and Regional Government

57. General

1. The financial relations between the Ethiopian Federal Government and the Regional Government shall include the yearly budget subsidiary appropriated to the Region by the Ethioian Federal Government.
2. With regard to the budget subsidiary appropriation received by the Regional Government from the Federal government, it shall maintain accounts pursuant to the Finance administration Law of the Federal government and shall provide a report to the Federal government.

58. Local Loans

1. The Regional Government shall provide to the Federal Government all necessary information that enables the Federal Government to limit the amount of money the Region can appropriate through loans.
2. Unless and otherwise the loans to be secured by the Regional Government is appropriated from sources other than the Ethiopian National Bank, any payment effected on money received as loans shall be administrated by the Ethiopian National Bank.
3. Where the loans appropriated are received from sources other than the Ethiopian National Bank, an administrative system jointly agreed by the Regional Government and the Ministry of Finance of the Federal Government Shall be made effective.

59. Foreign Exchange

The Office shall provide to the Ministry of Finance of the Federal Government the appropriate information with respect to the foreign exchange needs of the Regional Goveornment.

PART THIRTEEN
Miscellaneous Provisions

60. Directives

The office may issue directives to put this Proclamation into effect.

61. Loss of Public Funds and Property

The Regional Executive Committee may, based on the recommendations received from the Office, issue Regulations:

(a) prescribing the actions to be taken when there are losses of any manner to public funds or property,

(b) the manner of charging losses of public funds against the budget appropriated,

(c) the manner of reporting and recording in the public accounts of any loss of public property or funds refered to under sub-Article (a) of this Article.

62. Offences and Punishment

1. Every public employee or appointee employed in any public office to collect, manage or disburse public funds who:

(a) receives any payment for the performance of his official duties except provided by law;

(b) defrauds the funds of the Regional Government or colludes or conspires so that another person defrauds thereof;

ሐ) በሌላ ማናቸውም ሰው ሕጉ እንዲጣስ ሆን ብሎ የፈቀደ፣

መ) ገቢን በመመዝገብ ወይም የምስክር ወረቀት በመስጠት ሥራ ላይ የተሠማራ ሆኖ ሣለ በፈቃደኝነት በማናቸውም መንገድ ሀሰተኛ የሆነ መረጃን በመዝገብ ላይ ያሰፈረ፣ ሀሰተኛ የምስክር ወረቀት የፈረመ ወይም ያዘጋጀ፣

፩. እንደሆነ ከብር ፳፭ ሺ በማያንስና ከብር ፴፭ ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከ፲ ዓመት በማያንስ ከ፲፭ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፪. የመንግሥት ገንዘብ ለመሰብሰብ ለማስተዳደር ወይም ክፍያ ለመፈጸም በማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው ማንኛውንም ክፍያ ለማስቀረት ወይም መጠኑን ለማሻሻል ወይም ሕግ መጣሱን በሚመለከት የሚቀርቡ የክስ አቤቱታዎችን ለማስቀረት በቀጥታ ወይም በተዘዋወሪ በስጦታ ወይም በሌላ መልክ ገንዘብ ወይም ዋጋ ያለው ነገር እንዲሰጠው የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም ለመቀበል የሞከረ እንደሆነ ከብር ፳፭ ሺ በማያንስና ከብር ፴፭ ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከ፲ ዓመት በማያንስና ከ፳፭ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፫. የመንግሥት ገንዘብ ለመሰብሰብ፣ ለማስተዳደር ወይም ክፍያ ለመፈጸም በማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን የመተላለፍ ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈፀሙን እያወቀ ለበላይ ኃላፊዎች ሪፖርት ያላደረገ እንደሆነ ከብር ፲ ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከ፭ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፬. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፬ የተደነገገው በመተላለፍ የተፈቀደ በጀት መኖሩን ሳያረጋግጥ ማንኛውንም ውል የተፈራረመ ወይም እንዲፈረም ያደረገ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ኃላፊ ከብር ፭ሺ በማያንስና ከብር ፳ ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከ፭ ዓመት በማያንስ ከ፲ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፭. ማናቸውም ሰው የመንግሥት ገንዘብ ከመሰብሰብ፣ ከማስተዳደር ወይም ክፍያን በመፈፀም ሥራ ላይ በተሠማራ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው፣

ሀ) የቀረበለትን ውሣኔ በመጠበቅ ላይ ያለውን ጉዳይ ወይም በስራ ኃላፊነቱ ምክንያት ሊቀርብለት በሚችል ጉዳይ ላይ የሚሰጠውን ውሣኔ ወይም የሚወሰደውን እርምጃ ለማዛባት ወይም፣

ለ) በመንግሥት ገቢ ላይ የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈጽም ወይም ድርጊቱ ሲፈጽም እንዲረዳ ወይም እንዲተባበር ወይም ለድርጊቱ መፈጸም ሁኔታዎች ለማመቻቸት ወይም እንዲፈቅድ ለማድረግ በማሰብ፣

ሐ) ጉቦ ለመስጠት ቃል ከገባለት፣ ካቀረበለት ወይም ከሰጠው ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱ ሲረጋገጥ በጉቦ መልክ ያቀረበውን ወይም የሰጠውን ገንዘብ ሦስት እጥፍ የገንዘብ መቀጮ እና ከ፲ ዓመት በማያንስ እና ከ፲፭ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል።

(c) deliberately permits an offence by any other person;

(d) in any manner wilfully makes fraudulent entires in records, or sign or prepares fraudulent certificates where it is the duty of that person to make entires or issuance of certificates,

shall be liable to a fine not less than Birr 25,000 and not more than Birr 35,000 and to a rigorous imprisonment not less than 10 years and not more than 15 years.

2. Any person appointed or employed in any public office to collect, manage or disburse public funds who demands, receives or attempts to receive, directly or indirectly, in the form of gift or otherwise, money or other thing of value, to cancel any payment or to alter the amount or to cancel the institution of complaints related to contraventions of the law shall be liable to a fine not less than Birr 25,000 and not more than 35,000 and to a rigorous imprisonment not less than 10 years and not more than 25 years.

3. Any person appointed or employed in any public office to collect, manage or disburse public funds who, having knowledge of contraventions or fraudulent offences made against this Proclamation or Regulations issued under this Proclamation, fails to make report to superior executives shall be labile to a fine not more than Birr 10,000 and a rigorous imprisonment not more than 5 years.

4. The head of a public office who, in contravention of Article 54 of this Proclamation concludes or auhtorizes the conclusion of a contract without acertaining the availability of an appropriated fund, shall be liable to a fine not less than Birr 5,000 and not more than 20,000 and a rigorous imprisonment of not less than 5 years and not more than 10 years.

5. Any person who promises, offers or gives bribe to any appointee or employee of a public positioned to collect, manage or disburse public funds,

(a) to influence the matter presented for him which awaits his decision or the decision or the actions to taken on the matter to be presented for him due to his official duty, or,

(b) to execute a fradulent offence or aid the execution of the offence or participation thereof on the revenue of the Government, or to allow opportunities for the commission of the same shall, upon conviction, be liable to a fine of money, the amount of which is three times that offered or given as bribe and a rigorous imprisonment of not less than 10 years and not more than 15 years.

፮· በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፭ የተዘረዘሩትን ጥፋቶች በመፈጸም ተግባር ውስጥ የተሣተፈና ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈጸመው ጥፋት እና ስለተባባሪዎቹ ሚና ጠቃሚ መረጃ የሰጠ ሰው በዚህ ሕግ መሠረት ከሚቀርብበት ክስ በፍትህና አቃቢ ሕግ ቢሮ ምህረት ሊደረግለት ይችላል።

፷፫· <u>የሂሣብ ሰነዶችን ስለማየት፣</u>

፩· ቢሮው በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የማናቸውንም የመንግሥት መ/ቤት የሒሣብ መዛግብቶች፣ መጻሕፍት፣ ወረቀቶች፣ የሂሣብ ሰነዶች እና መረጃዎች ለማየት ያልተገደበ ሥልጣን አለው።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ቢኖርም ለክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ አካላት ሪፖርት የማያደርጉ የመንግሥት መ/ቤቶች የሂሣብ መዛግብትን፣ ወረቀቶችን፣ የሂሣብ ሰነዶችን እና መረጃዎችን ቢሮው ለማየት የሚችለው ከእነዚህ የመንግሥት መ/ቤቶች ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት ይሆናል።

፷፬· <u>የውክልና ሥልጣን ስለመስጠት</u>

ለዚህ አወጅ አፈጻጸም ሲባል የቢሮው ኃላፊ ለመ/ቤቱ ባለሥልጣኖች ወይም ለሌሎች ቢሮዎች ባለሥልጣኖች ሥልጣኑን በውክልና ለመስጠትና ውክልናው ተፈጻሚ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች ለመወሰን ይችላል።

፷፭· <u>ሰነዶችን ስለመጠበቅ</u>

የክልሉን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እያንዳንዱ የሂሣብ ሰነድ መጠበቅ ያለበት ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ የሚገልጽ ደንብ ያወጣል።

፷፮· <u>የተሻሩ ሕጎች</u>

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፷፯· <u>የመሸጋገሪያ ውሣኔ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫፣ ፲፬፣ ፲፯፣ ፵፩፣ ፵፪፣ ፵፫፣ ፵፭፣ ፵፯፣ ፶፫፣ ፷፩ እና ፷፭ የተደነገጉት ቢኖሩም የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ደንብ እስከሚያወጣ ድረስ እነዚህ ጉዳዮች በተመለከተ በሥራ ላይ የሚገኙ መመሪያዎች እና አሠራሮች ከዚህ አዋጅ ጋር ተቃራኒ ካልሆኑ በስተቀር ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፷፰· <u>የተፈጻሚነት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል

እስሜኤል አሊ ቤሮ
የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ርዕሰ መስተዳድር

6. Any person who participates in the commission of offences listed under sub-Article (5) of this Article and who provides essential information with respect to offence committed and the role of his collaborators before the case is presented to the court, may be pardoned by the Office of Justice and Prosecution from charges to be instituted under this law.

63. *Access to Financial Documents*

1. The Office shall, in the execution of its responsibility given under the law, have unrestricted power to examine financial record, books, paper, financial documents and information of any public office.
2. Notwithstanding sub-Article (1) of this Article, the financial records, papers, financial documents and information of public offices which make a report to executive bodies of the Regional Government shall be accessible to the Office pursuant to an agreement made with these public offices.

64. *Delegation of Powers*

For the purpose of the execution of this Proclamation, the head of the Office may delegate his powers to the officials of his office or to the officials of other offices and define the circumstances in which such powers may be exercised.

65. *Retention of Documents*

The Regional Executive Committee shall issue Regulations that limits the duration of time for the retention of each financial document.

66. *Repealed Laws*

No law, regulations directives or practices inconsistent with this Proclamation shall have effect on matters provided for in this Proclamation.

67. *Transistory Provisions*

Notwithstanding the provisions of Article 13,14,17,41,42,43,45,47,53,61 and 65 until Regulations are to be issued by the Regional Executive Committee, directives or practices with respect to such matters shall remain effective in so far as they are not inconsistent with this Proclamation.

68. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the date of its publication in the Negarit Gazeta.

Esmail Ali Sero
President of the Afar National Regional State

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE

7

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ
AFAR REGION NEGARIT GAZETA

AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፯
አይሳኢታ – ሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፺፩

በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 7
AYSAITA – 8th July, 1999

ማውጫ

የአፋር ዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና የእርሻ ልማት ፣ የወረዳ ግብርናና የተቀናጀ የገጠር ልማት አገልግሎት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ... 8/1991 ... ገጽ ፩

CONTENTS

A Proclamation to Establish the Afar Permanent Environmental Rehabilitation and Agricultural Development, Woreda Farming and Coöprated Rural Development Service Commission .... Page 1

የአፋር ዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና የእርሻ ልማት፣ የወረዳ ግብርናና የተቀናጀ የገጠር ልማት አገልግሎት ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በአፋር ክልል ከፍተኛ የአካባቢ መራቆት የተባባሰ መሆኑንና ኅብረተሰቡ ለአስከፊ የገጠር ልማት አገልግሎት እጥረት የተጋለጠ በመሆኑ፣ በክልሉ የአካባቢ ተሀድሶ በመፍጠርና ወረዳን ያማከለ የተቀናጀ የገጠር ልማት አገልግሎት በመዘርጋት የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ፣

የክልሉ የኅብረተሰብ በምግብ ራሱን እንዲችልና በክልሉ ብልፅግናን ለማፋጠን፣ በኢኮኖሚ መስኮች መካከል ያለውን ትስስር በየወረዳው ማጠናከር በማስፈለጉ ፣ ክልሉ ካለበት ኋላቀር የእድገት ደረጃ ለማላቀቅ እና ኅብረተሰቡ በዋነኛነት የሚፈልጋቸውን የልማት ሥራዎች ለማስፋፋት ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ፕሮግራም የተናዘበ መከተል በማስፈለጉ፣ የአፈር የግብርናና የተፈጥሮ ሀብት ከተጋለጠበት ከፍተኛ ብክነትና ጥፋት አድኖ ማልማትና ጥቅም ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘት ፣ የገጠሩን ኅብረተሰብ ገቢውን ማሳደግ፣ የሥራ ዕድልን መፍጠር፣ የቴክኒክ ሙያና የሥራ ዕውቀቶችን ማስፋፋት እንዲሁም ከብት አርቢውን ኅብረተሰብ ወደ ተሰባሰበና ቋሚ የኑሮ ሁኔታ እንዲመጣ ማድረግ መርዳት አስፈላጊ በመሆኑ፣ የእርሻ ምርት ለማሳደግና በምግብ ራስን ለመቻል አስተማማኝ የአካባቢ ተሀድሶ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ስለሆነ ፣ የግብርና ምርትና ምርታመነትን ለማሳደግ በእርሻ እና በእንስሳት እርባታ ከገጠር ልማት ጋር ማቀናጀት አስፈላጊ በመሆኑ፣ ይህንን ለመፈፀም ራሱን የቻለና ከገጠር ከብት አርቢ ኅብረተሰብ ጋር የሚሠራ የማኔጅመንት አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በአፋር ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ ቁጥር ፪.፪ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

A PROCLAMATION TO ESTABLISH THE AFAR PERMANENT ENVIRONMENTAL REHABILITATION AND AGRICULTURAL DEVELOPMENT, WOREDA FARMING AND COOPRATED RURAL DEVELOPMENT SERVICE COMMISSION

WHEREAS, the growing environmental degradation in the Afar Region is orsening and the people is faced with a worsening lack of rural development service;

WHEREAS, it is necessary to improve the living standards of the people by creating environmental rehabilitation in the Region and through implementing an efficient Woreda centered development service;

WHEREAS, it is needed make the people of the region self-sufficient in food and to facilitate prosperity in the Region;

WHEREAS, it is necessary to strengthen the existing tie of cooperation among the economic fields in each Woreda;

WHEREAS, it is necessary to follow a programme that is compatible with the objective situation of the Region intended to free the Region from its backward development standard and to facilitate the major developmental activities needed by the society;

WHEREAS, it is found necessary to rescue develop and put to use the agricultural and natural resources to the Afar Region from the excessive misse and destruction is faced with;

WHEREAS, it is necessary to increase the income of the rural people, to create job opportunities, to facilitate technical professions and job creating education in addition to supporting the pastoral society to lead a collective and settled life style;

WHEREAS, it is necessary to utilize reliable environmental rehabilitation method intended to increase agricultural produce and self sufficiency in food;

WHEREAS, it is necessary to coordinate farming and animal husbandry with rural development in order to improve agricultural produce and productivity;

WHEREAS, to implement this it is found necessary to establish an independent management body that works with the rural animal breeding soceity; pursuant to Article 47 (2.2) of the constitution of the Afar National Region, it is hereby proclaimed as follows.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3.50

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪. ክፍል አንድ
ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአፋር ዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና እርሻ ልማት፣ በወረዳ ግብርና የተቀናጀ የገጠር ልማት አገልግሎት ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር ፰/፲፱፻፺፩ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉን አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩ኛ/ "ኮሚሽን" ማለት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን ወይም እንደ አግባብ የአፋር ዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና እርሻ ልማት፣ በወረዳ ግብርና የተቀናጀ የገጠር ልማት ኮሚሽን ማለት ነው።

፪ኛ/ "ፕሮግራም" ማለት የዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና እርሻ ልማት፣ በወረዳ ግብርና የተቀናጀ የገጠር ልማት ፕሮግራም ማለት ነው።

፫ኛ/ "የአገልግሎት" ማለት የኮሚሽኑ ፕሮግራም አገልግሎት ማለት ነው።

፬ኛ/ "የተቀናጀ የገጠር ልማት" ማለት በገጠር የኢኮኖሚ መስኮች መካከል ያለውን ትስስርና ብልፅግና ማለት ነው።

፭ኛ/ "ኮሚሽን" ማለት የአፋር ክልል የዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና እርሻ ልማት፣ በወረዳ ግብርና የተቀናጀ የገጠር ልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር ማለት ነው።

፮ኛ/ "ግብርና ሥራ ማለት" በግብርና ልማት በአግሮ ኢንዱስትሪ እና በግብርና አገልግሎት መስክ የሚካሄድ ሥራ ነው።

* "የግብርና ልማት ማለት" የቋሚና የዓመታዊ ሰብሎች ልማት የእንስሳትና የዓሣ ሀብት ልማትና ተዋፅኦ የደን የዱር አራዊት ልማትና ተዋፅኦ ነው።
* "የአግሮ ኢንዱስትሪ" ማለት ማናቸውም ሰው የራሱን የግብርና ተረፈ ምርትና በተጨማሪ ለተጠቃሚው በሚያመች ዘዴ በፋብሪካው አደረጃጀትም አቀነባብሮ ለማቅረብ የሚያካሂደው የሥራ መስክ ነው።
* "ግብርና አገልግሎት" ማለት በግብርና ሥራ ለተሠማሩ የአገልግሎት ክፍያ በመቀበል የቴክኒክ አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋም የሥራ መስክ ነው።

፯ኛ/ "የተፈጥሮና የእርሻ ሀብቶች" ማለት የአፈርና ውኃ፣ ግጦሽ፣ አትክልት ፣ እንስሳትና ሌሎች ለገጠር ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ የተፈጥሮ እና የእርሻ ሀብቶች ማለት ነው።

፰ኛ/ "ተጠቃሚ" ማለት ኑሮው በከብት እርባታ ፣ በእርሻ ሥራ፣ በሌላ በማንኛውም የግብርና ሥራ ወይም የገጠር ሀብት የተመሠረተና በኮሚሽኑ የመስኖ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆነ ሰው ወይም ቡድን ማለት ነው።

፱ኛ/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

፲ኛ/ "ክልል" ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልል ማለት ነው።

፲፩ኛ/ "መንግሥት ማለት" የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ወይም እንደአግባቡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ማለት ነው።

፲፪ኛ/ "ወረዳ" ማለት ማንኛውም በአፋር ብሔራዊ ክልል ውስጥ እውቅና የተሰጠው ወረዳ ማለት ነው።

፲፫ኛ/ "ዘላቂ እርሻ" ማለት የተፈጥሮ እና የእርሻ ሀብቶች ሕዝብ በአግባቡ እንዲተዳደር፣ እንዲጠቀምበትና እንዲያሳድገው እያደረገ የሚቀጥለው ትውልድ በተመሳሳይ መንገድ ጠብቆና አሳድጐ መጠቀም ማለት ነው።

PART ONE
GENERAL

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as "A Proclamation to establish the Afar Permanent Environmental Rehabilitation and Agricultural Development, Woreda Farming and coordinated Rural Development Service Commission Number 8/1999".

2. *Definition*

Unless the context requires otherwise in this Proclamation.

1. "Commission" means the African Economic Commission, or depending on the context the Afar Permanent Environmental Rehabilitation and Agricultural Development Woreda Farming and coordinated Rural Development Commission.
2. "Programme" means the Permanent Environmental Rehabilitation and Agricultural Development, Woreda Farming and Coordinated Rural Development Programme.
3. "Service" means the service of the programme of the Commission.
4. "Coordinated Rural Development" means the tie and prosperity existing among rural economic fields.
5. "Commissioner" means the commissioner of the Afar Permanent Environmental Rehabilitation and Agricultural Development Woreda Farming and coordinated Rural Development Commission.
6. "Agricultural Work" means an activity performed in the fields of agricultural development, agro-industry and agricultural service.
   "Agrici'tira' Development" means the production of continuous and annual crops, fish products and resources and wildlife development.
   "Agro-industry" means the field of activity undertaken by any person an industrially organizing and processing his surplus products and additionally, in a manner convenient to the consumer.
   "Agricultural Service" means a field of activity established to provide technical assistance for those engaged in agricultural works in return for service charges.
7. "Natural and Agricultural Resources" means soil and water, pastoral land vegetation, animals and other natural and agricultural resources which are imperative to rural life.
8. "User" means a person or group whose life isbased on animal husbandry, farming work, any other agricultural work or rural resources and who is the beneficiary of the irrigation programme of the commission.
9. "Person" means any natural person or an entity that has legal personality.
10. "Region" means the Afar National Region.
11. "Government" means the Government of the Afar National Region or depending on the context the Government of the Ethiopian Federal Democratic Republic.
12. "Woreda" means any Woreda that is given such recognition in the Afar National Region.
13. "Permanent Farm" means the utilization of natural and agricultural resources through the prope administration, appropriation and development with a view to succtaining and improving it for similar use to the next generation.

፲፬ኛ/ "ኮንፈረንስ" ማለት ክልላዊ የተጠቃሚዎች ኮንፈረንስ ማለት ነው።

፲፭ኛ/ "ቦርድ" ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመ የኮሚሽኑ ቦርድ ማለት ነው።

፫· ስለመቋቋም፤/

፩· የአፋር ዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና እርሻ ልማት ፤ በወረዳ የተቀናጀ የገጠር ልማት ኮሚሽን የህግ ሰውነት ያለውን ራሱን የቻለ የመንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚና ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል።

፬· የኮሚሽኑ ዓላማዎች፡

፩· የመስኖ እርሻ እንዲስፋፋ በማድረግ የምግብ እጥረትን ማቃለል፣

፪· በገደብ ተፋሰስ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ እንዲ ካሄድ ማድረግ፣

፫· መሠረታዊ የሆኑ ማህበራዊ አገልግሎቶችን በማቅረብና በማጠናከር በዋነኝነት የገጠሩን ህዝብ የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፣

፬· የኢኮኖሚ መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶችን በመዘር ጋትና በማቅረብ የከብት አርቢው ህብረተሰብ ምርታማ ነትና የማግኘት አቅም ማሳደግ፣

፭· የወረዳው ህብረተሰብን መሠረት ያደረጉ ፕሮጀክቶችን የመለየት፣ የማዘጋጀትና የመተግበር፣ የማስተዳደርና የመ ንከባከብ ዘይቤን በህብረተሰቡ ውስጥ ማራመድ፣

፮· ቀጣይነት ያለው አነስተኛ ብድር ለወረዳ ህብረተሰብ መስጠት የሚችሉ ብድር ሰጭ ድርጅቶችን እንዲፈጥሩና እንዲዳብሩ መርዳት፣

፯· ህብረተሰቡን አግዘው የሚሰሩ መሠረታዊ ድርጅቶችንና ማህበረሰቦችን በፕሮጀክት ሥራዎች ታክኒካዊና የሥራ አመራር ብቃት እንዲዳብሩ መርዳት፣

፰· የወረዳ መሠረተ ልማቶች፣ አገልግሎቶች እና አውታሮች ማጐልበት እና ማጠናከር፣

፱· ተጠቃሚዎች ፕሮግራም፣ ዕቅድና በጀት በማውጣትና በመገምገም ችግሮችን በማጤን የግድብ ቦታዎችን በመመሪያ በግድብ ሥራዎችና በጥበቃ እንዲሁም መስኖውን በማስተዳደር ተገቢ ተሣትፎ እንዲኖረው ማድረግ፣

፲· የህዝብ ተሳትፎ ማጐልበት፣ የአካባቢ ተሀድሶ መፍጠርና የተቀናጀ ልማት በወረዳ ማማካል፣

፭· የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር፡

፩· የኮሚሽኑ ሥራዎችን በሚመለከት ሕጐች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ያወጣል ሲጸድቅ ሥራ ላይ ያውላል፣

፪· የግድቦችንና የመስኖ አውታሮችን ዲዛይን ይሰራል፡፡ ያንጻል፣

፫· ከተጠቃሚዎች ከወረዳ እና ጣቢያ መስተዳድር አካላት ጋር በመተባበር የግድቦችና የመስኖ አውታሮች ደህንነት ይከታተላል፤ እድሳት የሚያስ ፈልጋቸው እንዲታደሱ ያደርጋል፣

፬· በግድቦችና ተፋሰስ ሊሰሩ የሚገባቸውን የአፈርና ውሃ ጥበቃ ዲዛይኖች ለመሥራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፣

፭· በህዝብና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካሎች ሊሰሩ የታቀዱ የእርሻ ግድቦች ዲዛይንና ግንባታ ስተንዳርድ ይቆጣ ጠራል፣

፮· የተጠቃሚ ከብት አርቢዎችና ገበሬዎች ምርታማነት እንዲጨምር ግድቦችና የመስኖ አውታሮች እንዲታደሱ እና በአካባቢው ሊደርስ የሚችል ጉዳት ለመቆጣጠር ከተለያዩ መንግሥታዊ አካሎች ጋር በተመባበር ይሰራል።

14. "Conference" means Regional users conference.

15. "Board" means the Board of the Commission set up under this Proclamation.

3. ***Establishment***

1. The Afar permanent Environmental Rehabilitation and Agricultural Development Woreda coordinated Rural Development Commission which has legal personality is established under this Proclamation as an independent governmental office.
2. The commission shall be accountable to the Regional Executive committee and the President.

4. *Objectives of the Commission*

1. Lessening food deficiency through the development of irrigation farming,
2. Implementing natural resovrce development and preservation through constructed reservoirs and streams,
3. Improving the life standards of mainly the rural population by providing and strengthening the basic social services,
4. Increasing the productivity and earning capacity of the animal breeding population by establishing and providing economic infrastructure and services.
5. Dessiminating to the population the attitudes of differentiation, preparation implementation administration and preservation of projects that are targeted to the people of the Woreda,
6. Facilitating the creation and growth of credit rendering organizations which are capable of providing small scale loans to the people of the Worede continuously,
7. Helping basic organizations that support the society and the population to boost their technical and managerial skills through work undertaken in projects,
8. Boosting and strengthening infrastructures, services and sectors in Woredas,
9. Ensuring the users to have appropriate participation inoutining and supervising programmes, plans and budget, identifying problems; in directing place for resevoirs; in construction and maintenance of reservoirs and administration of irrigation,
10. Boosting popular participation; creating invironmental rehabilitation and centralizing coordinated development in Woredas,

5. *Powers and Dutes of the Commission*

1. Proposes lows, policies and strategies related to the works of the Commission, implements them when ratified;
2. Designes and constructs reservoirs and irrigation complexes;
3. Follows the safety of reservoirs and irrigation complexes in cooperation with users Woreda and station administrative bodies; arranges maintenance when necessary;
4. Cooperates with concerned bodies which work on methods of preservation of soil and water on reservoirs and streams;
5. Controls the standards of designes and construction of agricultural dams planned to be performed by the people and non-governmental bodies;
6. Works in cooperation with various governmental bodies in repairing reservoirs and irrigation complexes to increase the productivity of user-pastoral breeders and farmers and to control the damage that could result on the environment;

፯· ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር
ህዝቡ ስለግድብና መስኖ በእድሳትና ግንባታ የተጠቃሚዎች ሚና እንዲሁም የውሀ የእርሻ የግጦሽና የመስኖ አጠቃቀም እንዲያውቅ ያደርጋል።

፰· አቅም ለመፍጠር የሚያስችሉ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚዛመዱ የሌሎች አገሮች ልምድና ቴክኖሎጂ ያጠናል፤

፱· ከተጠቃሚ የክልሉ ከብት አርቢዎችና ገበሬዎች ጋር ስለ ግድብ ቦታ አመራረጥ ግንባታ፣ የመሬትና፣ ውሃና የግጦሽ አጠቃቀም፣ የግድብና መስኖ መዋቅር እድሳትና እንክብካቤ፡ የዕዳ አከፋፈልና ለሚፈናቀሉ ገበሬዎችና ለሚሰባሰቡ ከብት አርቢዎች መፍትሄ በሚሰጥ አግባብ ባላቸው ህጎች መመሪያዎችና ደንቦች መሠረት ስምምነት ያደርጋል፤

፲· በወረዳ ማዕከልነት ሊከናወኑ መሠረታዊ ማህበራዊ እና ኢኮሚያዊ አገልግሎቶችን ለማቋቋምና ለማጠናከር ህዝባዊ ተሳትፎ ባላቸው ፕሮጀክተር አማካኝነት እርዳታና ብድር መስጠት፤

፲፩· የሥልጠና ፕሮግራሞች ለህብረተሰቡ በማዘጋጀት መሠረታዊ የህብረተሰቡ አቅም ማጐልበት፤

፲፪· ሴቶች ማንኛውም የፕሮጀክት ሥራ እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ማበረታታት፤

፲፫· የንብረት ባለቤት መሆን፤

፲፬· ውል ማዋዋል፤

፲፭· በስም የመክሰስና መከሰስ፤

፲፮· ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ማከናወን፤

፮· <u>ዋና ጽህፈት ቤት</u>
የኮሚሽኑ ዋና ጽህፈት ቤት ሰመራ ይሆናል፤ ሆኖም ግን እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች አካባቢዎች ቅርንጫፍ ሊኖሩት ይችላል።

፯· <u>ሕጋዊ ሰውነት፤</u>
ኮሚሽኑ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ ንብረት የመያዝ ውል የመዋዋል፤ የመክሰስ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ተግባሮችን የመፈጸም ሥልጣን አለው።

፰· <u>የሠራተኛ አስተዳደር፤</u>
የኮሚሽኑ ሠራተኞች ቅጥርና አስተዳደር በአሰሪና ሠራተኛ ህግ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።

፱· <u>ኮሚሽኑ፡</u>
፩· በክልል ደረጃ የተጠቃሚዎች ኮንፈረንስ
፪· ቦርድ
፫· በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሾም ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነር፣
፬· ሌሎች አስፈላጊ ሠራተኞች፣
፭· የወረዳ ዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና የእርሻ ልማት፣ የተቀናጀ የገጠር ልማት ኮሚቴ፡
፮· የግድብ ተጠቃሚዎች ጠቅላላ ጉባኤ፤
፯· የግድብ ዘላቂ የአካባቢ ተሀድሶና የእርሻ ልማት ኮሚቴ ይኖሩታል፤

ክፍል ሁለት
ስለኮንፈረንሱ ቦርድ

፲· <u>የኮንፈረንሱ አባላት</u>
፩· ኮንፈረንሱ በኮሚሽኑ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆኑ ወረዳዎች የሚወክሉ ወንዶችና ሴቶች ወጣት ገበሬዎች አባላት ይኖሩታል፤
፪· የኮንፈራንሱ ሊቀመንበር፣ ም /ሊቀመንበርና ፀሐፊ ይኖሩታል፤
፫· የአካሎች ብዛት አወካከልና የሥራ ጊዜ በመመሪያ ይወሰናል።

7. Teaches the people the benefits of reservoirs and irrigation, the role of users in maintenance and construction in addition to the utilization of water, agriculture, grazing land and irrigation,
8. Exames the practice and technology of other countries which could create capacity that are related to the objective situation of the Region;
9. Concluds agreements pursuant to the appropriate laws directives and regulations on the choice and construction of areas of reservoirs with users, animal breeders and farmers of the Region, on the utilization of land, water and pasteur. on repair and maintenance of reservoirs and irrigation structurs; on payment of debts and rendition of solutions of dislocated farmers and settling animal breeders;
10. Provides aid and loans to popular projects performed to establish and strengthen basic social and economic services which are Woreda centered;
11. Boosts the basic capacity of the population by preparing training programmes to the populations;
12. Mobilizes women to participate in all project undertakings;
13. Owns property;
14. Concludes contracts
15. Sues and be sued on its own behalf;
16. Performs other activities necessary for the fulfillment of its goals;

6. *Head Office*
The lead office of the Commission shall be situated in Sammera however it may have branches in other areas if necessary.

7. *Legal Personality*
The commission shall, being a body with have legal personality, have the power to own property, to conclude contracts, to sue and to execute other necessary activities.

8. *Administration of Workers*
The employment and administration of the workers of the Commission shall be governed by Labor Law.

9. *The Commission*
The Commission shall have the following;
1. Users' Conference on the Regional level;
2. A Board;
3. A Commissioner and deputy commissioner to be appointed by the executive committee on the recommendations of the Regional President;
4. Other necessary staff;
5. Woreda Permanent Environmental Rehabilitation and Agricultural Development; coordinated Rural Development committee;
6. Reservoir users General Assembly
7. Reservoirs Permanent Environmental Rehabilitation and Agricultural Development Committee;

PART TWO
CONFERENCE AND BOARD

10. *Members of the Conference*
1. The Conference shall have, as members Woredas and represented young male and female farmers which are benficieries of the programmes of the Commission.
2. The conference shall have a chairman: a vice chairman and a secretary.
3. The number of members, the manner their representation and duration of service shall be defined by a directive;

፲፩. <u>የኮንፈራንሱ ተግባርና ኃላፊነት፣</u>

፩. የኮሚሽኑ ስትራቴጂ ፣ ፖሊስና አላማዎችን በተመለከተ ተወያይቶ ሃሣብ ያቀርባል፣

፪. የሰው ሀይል ማቴሪያልና ገንዘብ ማሟላትና ማስማራት በግደብ ሥራ ምክንያት የሚከተል የውሃ ፣ የግጦሽና የመሬት አጠቃቀም መዛባት እንዲሁም ሌሎች ከኮሚሽኑ ጋር የተያያዙ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ችግሮችን በተመለከተ ተወያይቶ መፍትሔ ያቀርባል።

፫. በኮሚሽኑ ዓመታዊ በጀትና ዕቅድ ተወያይቶ ገምግሞ አስተያየት ይሰጣል።

፬. የፈሰሰውን የኢንቨስትመንት ዕዳ ለመመለስ ጥገናና የሰው ሀይል አጠቃቀም በተመለከተ ተወያይቶ መፍትሔ ሀሳብ ያቀርባል ፣ በመንግሥት የሚወጡ ሕጎችና ደንቦች ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በሚያጠናከር መልኩ የክልሉ መንግሥት የሚያወጣቸው አዋጆችና ደንቦች የማይቃረን የአካባቢ ስራቶችን ያወጣል፤

፭. እንደ አስፈላጊነቱ ከውጭ ኦዲተር በመሰየም የተጠቃሚዎች የኢንቨስትመንት ዕዳ መመለስ በተመለከተ እንዲመረመር ያደርጋል፣ ሪፖርቱን ተወያይቶ ያፀድቃል።

፮. ከአባላት መካከል የቦርድ አባላት ይመርጣሉ።

፯. ተጠቃሚዎች በማኅበር ተደራጅተው የሚሠሩበትን መንገድ ይጠቁማል፣

፰. የቦርዱን ዓመታዊ ሪፖርት ይገመግማል።

፱. ወረዳን ያማከለ የተቀናጀ የልማት ጥናትና ምርምር ሰፊ የህብረተሰብ ተሳትፎ ስለሚታቀፍበት መንገድ ይነድፋል።

፲፪. <u>የኮንፈራንሱ ስብሰባ</u>

፩. ኮንፈራንሱ በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል ሆኖም ግን ቦርዱ ጥሪ ሲያደርግ ልዩ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

፪. ሁለቱ ሦስተኛ የኮንፈራንሱ አባላት ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

፫. የኮንፈራንሱ ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ ያልፋል ድምጽ እኩል ሲሆን ሰብሣቢ ያለበት ወገን አሸናፊ ይሆናል፤

፬. የኮንፈራንሱ አብላጫ ድምጽ ውሣኔ ከነባራዊ እውነታ የሚፃረር እና ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚቃረን ከሆነ የአብላጫ ድምጽ ውሣኔው ውድቅ ሆኖ ለጉዳዩ አግባብነት እና ከፍተኛ ብቃት ያላቸው አካላትና ሰዎች ጥልቅ እና ግልጽ ማብራሪያ በመስጠት የግንዛቤ ማስጨበጥ እና የሶሻል ኢንጂነሪንግ ተግባራት እንዲያከናውኑ ተደርጐ የኮንፈራንሱ አባላት እንደገና ድምጽ እንዲሰጡበት ይደረግና የኮንፈራንሱ አብላጫ ድምጽ የመጨረሻ አሸናፊ ውሣኔ ይሆናል።

፲፫. <u>የቦርድ አባላት</u>

ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

፩. ርዕሰ መስተዳድር ወይም ተወካይ........................ ሰብሣቢ

፪. ኮሚሽነር.. ምክትል ሰብሣቢ

፫. ም/ኮሚሽነር.. አባል

፬. በኮንፈረንሱ የሚወከሉ 12 የተጠቃሚ ተወካዮች...... አባላት

፭. የግብርና ቢሮ ኃላፊና የእርሻ ዘዴና ማኅበራት ማደራጃ ቡድን መሪ .... ”

፮. የውሃ ሀብት ቢሮ ሀላፊ .... አባል

፯. የሥራና ከተማ ልማት ማ/ኢ/ኃላፊ .... ”

፰. የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ.............................. ”

፱. የአደጋ መ/ዝ/ሣ/ማ/ጉ/ቢሮ ኃላፊ................................ ”

፲. ንግድ ፣ ኢንዱስትሪ ፣ ትራንስፖርትና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ.. ”

፲፩. የሥነ ህዝብ ጽ/ቤት ኃላፊ .... ”

11. Duties and Responsibilities of the Conference

1. Submits recommendation with regard to the strategies, policies and goals of he Commission after due deliberation;
2. Submits resolutions after due deliberation in relation to the fulfilment and mobilization of human, material and financial resources; for disorders of water pasteur and utilization of land which result due to the construction of reservoirs and for political and social problems which are connected with the Commission;
3. Submits a report on the annual budget and plan of he Commisssion after due deliberation and supervision.
4. Submits a resolution as to how used debt of investment, refair and human resources would be reimbursed; proposes environmental schemes by assessing that they are not contrary to the laws and regulation of the Regional government and persuant to the laws and regulations of the Federal Government by assessing the objective situation of he region,
5. Makes the accounts to be audited with respect to the payment of he investment debts of users by appointing external auditor where necessary; ratifies the report after deliberation;
6. Elects Board members from among its members;
7. Assists the users to mobilize by organizing associations .
8. supervises the annual report of the Board;
9. Outlines a scheme by which the research of the Woreda-centered coordinated development embraces wide popular participation;

12. Meeting of the conference

1. The conference shall convene once a year; however, it may have special meeting if called by the Board.
2. Two third members of the conference shall form a quorum.
3. The decision of the conference shall pass through majority vote; where there is a tie, the chairman shall have a casting vote.
4. Where the majority vote decision of the conference is contrary to existing realities and against objective situation, the majority vote decision shall be ruled out and after detailed and clear expalanations aimed at giving understandings and performances of social engineering have been done by relavant and highly qualified bodies and individuals, the member of the conference shall be made to give their votes again, such majority vote of the conference shall be final binding decision.

13. Members of the Board

The BOard shall have the following members:

1. The Regional President on a Delegate.........Chairmen
2. commissioner .... V/chairman
3. Deputy Commissioner ....Member
4. Twelve delegates of users represented to the conference .... Members
5. Head of the Bureau of Agriculture and Team Leader of Agricultural Systems and Organization of Association .... member
6. Head of Water Resources Berau.................. member
7. Head of works and Urban Berau ....''
8. Head of the Planning and Progamme Berau ....''
9. Head of the Disaster Prevention and Preparedness Berau ....''
10. Head of Trade, Industry, Transport and Tourism Berau ....''
11. Head of Population Office...................................''

፲፪· የማስታወቂያና የህዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት ኃላፊ................ ”
፲፫· የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ..................... ”
፲፬· የተጠቃሚ ወረዳ የከብት አርቢና የገበሬ ማኅበራት ተወካይ .... አባላት
፲፭· የተጠቃሚ ወረዳ የህብረተሰብ ተወካይ .... አባላት
፲፮· በክልሉ መንግሥት የሚወከሉ 3 የሥራ አስፈፃሚዎች አባላት
፲፯· የምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ/የሚወከል ፀሐፊ......... ፀሐፊና አባል

፲፬· <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩· የኮሚሽኑ ስትራቴጅ ፣ ፖሊሲዎች ህጐችና አሠራሮች ቀርጾ ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣
፪· የኮሚሽኑ ዓመታዊ እቅድና በጀት ለአፋር ክልል ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ለኮንፈራንሱ ያቀርባል ፣ አመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም ያፀድቃል፣
፫· የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ኮንፈራንሱ የሚሰጡት ውሣኔዎችና አስተያየቶች ይፈፅማል፣ የሁለቱም ውሣኔዎችና አስተያየቶች በሚቃረኑበት ጊዜ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ውሣኔ ተፈፃሚ ይሆናል፣
፬· በዚህ አዋጅና በክልሉ መንግሥት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የኮሚሽኑ መዋቅርና ቅርጽ የሠራተኛ አስተ ዳደር የግድብና የመስኖ ስርዓት ስታንደርድ መመሪ ያዎች ያወጣል፣
፭· የኢንቨስትመንት ዕዳ መመለስን በሚመለከት የአፈ ጻጸም መመሪያዎች ያወጣል፣
፮· የቦርዱ ተጠሪነት ለክልል ሥራ አስፈፃሚና ለርዕሰ መስተዳደር ይሆናል፣
፯· ቦርዱ ከላይ የተጠቀሰው ዝርዝር ሁኔታ ሣይወሰን፣ የኮሚሽኑ አጠቃላይ እንቅስቃሴ በተቀላጠፈና በሰከነ ሁኔታ ሊፈፀም ይችል ዘንድ በማንኛውም ደረጃ ከሚገኙት ተቋማትና መንግሥታዊ አካላት ትብብር ያስገኛል፣
፰· ኮሚሽኑ በሚመለከቱ ሌሎች የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ውሣኔ ይሰጣል።

፲፭· <u>የቦርድ ስብሰባ</u>

፩· ቦርድ በሶስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል ሆኖም ግን ኮሚሽነሩ የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳደር ወይም የቦርዱ ግማሽ አባላት ጥያቄ ሲያቀርቡ ተጨማሪ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
፪· ሁለት ሦስተኛው የቦርዱ አባላት ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፣
፫· የቦርዱ ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ ያልፋል እኩል ሲሆን የሶሻል ኢንጂነሪንግ ይካሄዳል ፣ የሶሻል ኢንጂነሪንግ ተካሂዶ እኩል ድምጽ ከሆነ ሰብሣቢ ያለበትን ወገን ውሣኔ ይሆናል፣
፬· ቦርዱ የራሱ የውስጥ ደንብና መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፣ ባወጣው የስብሰባ ስነሥርዓት ደንብም ይመራል፣
፭· ቦርዱ ከሩብ ዓመቱ መደበኛ ስብሰባ ውጭ በሰብሳቢው ጥሪ የቦርዱ አስቸኳይ ስብሰባዎች በማንኛውም ጊዜ ሊደረጉ ይችላሉ።

፲፮· <u>የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩· ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ የበላይ ሥራ አስፈፃሚ በመሆኑ የኮሚሽኑን ሥራዎች ይመራል፣
፪· የኮሚሽኑ ሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል ሲፈቀድም በሥራ እንዲውል ያደርጋል፣
፫· ኮሚሽነሩ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ኮሚሽኑን ይወክላል፣
፬· የቦርዱን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ሪፖርት ያቀርባል፣
፭· በቦርዱ የሚሰጡት ሌሎች ተግባሮች ይፈጽማል፣

12. Head of Information and Public Relations Office ...... ”
13. Head of the delegate of Women's Affairs .... ”
14. Delegate User Woreda Animal Breeders and Farmers Association .... ”
15. Delegate of the uses woreda population .... ”
16. Three Executives delegated by the Regional Government .... ”
17. The secretary of the Council/Delegated secretar- .... secretary and member ”

14.Powers and Dates of the Board

1. Submits to the Executive Committee of the Afar National Regioal government the strategies, policies, laws and procedures of the Commission which it has outlined;
2. Submits the annual plan and budget of the Commission to the Executive Committee of he Afar Regional Government and to the Conference; satifies the annual budget and work programme;
3. Executs the resolution and recommendations of the Regional Executive Committee; where the resolutions and recommendations of both contradicts, the decision of the Executive Committee shall prevail;
4. Issues directives on the structure and shape of the Commisssion, on the administration of worker, in the standards of reservors and irrigation systems persuant to this Proclamation and the directives issued by the Regional Government;
5. Issues execution directive related to the reimbursement of investment debts;
6. The accountability of the Board shall be to the Regional Executive Committee and the President;
7. The Board shall, without being comities to the detailed situations above, cooparate with institutions found on all levels and governmental bodies in order to execute the general activity of he commission efficiently and prudently;
8. Gives decisions on other policy matters that concern the commission;

15. Meeting of the Board

1. The board shall meet once in three months; however, it may hold additional meetings on the request of he commissioner; the President of he Afar Region or half the members of the Board.
2. Two thirds of the members of the board shall form a quorm.
3. The decision of the board shall pass through majority vote; where there is a tie, social engineering shall take place. If there is still a ties after social engineering, the decision of the group in which the chairman belongs shall prevail.
4. The board may issue its internal regulations and directives it is governed of he procedures of meetings it has issued;
5. Without prejudice to the quarterly regular meetings, the extraordinary meetings of the Board shall be held on the request of the chairman;

16. Powers and Duties of the Commission

1. The commissioner, being the executive head of he Commission, executes the works of the Commisssion,
2. Prepares the work programme and budget of he commission; executes it when ratified
3. Represents the Commission in relations the Commission makes with third parties;
4. Presents a report with regard to activities of the Board.
5. Executes other duties given by the Board;

፮· የኮሚሽነሩ ተጠሪነት ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል፡
፯· የኮሚሽኑ እንቅስቃሴዎች በክልሉ ውስጥ እንዲሰራጩ ማድረግ፣
፰· በአመልካቾች የሚቀርቡ ተዛማጅ ፕሮጀክቶችን መገምገምና ከውሣኔ ሃሣብ ጋር ለቦርዱ ማቅረብ፣
፱· በክልሉ የኮሚሽኑ እንቅስቃሴዎች በብቃት ለማከናወን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥልጣኑን ለኮሚሽኑ የወረዳ ምክር ቤት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡
፲· ለክልሉ ኮሚሽን ጽ/ቤት በተፈቀደው በጀት መሠረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤
፲፩· አግባብ ባለው ህግ መሠረት የኮሚሽኑ ሠራተኛ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል ፤
፲፪· ቦርዱና በሥራ አስፈፀሚ የሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ እንቅስቃሴዎች በኮሚሽኑ የአፈፃፀም ሂደት መሠረት በአግባቡ ተግባራዊ ለመሆናቸው ኃላፊ ይሆናል።
፲፫· በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 8 ለኮሚሽኑ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ይፈጽማል።
፲፯· ስለ ምክትል ኮሚሽነር
  ፩· ኮሚሽኑ አንድ ምክትል ኮሚሽነር ይኖረዋል።
  ፪· ኮሚሽነሩ በሌለበት ጊዜ ተተክቶ ይሠራል፣
  ፫· ተጠሪነቱ ለኮሚሽነሩ ይሆናል፤
  ፬· በአንቀጽ 16 ለኮሚሽነሩ የተሰጠ ሥልጣንና ተግባር በማስፈፀም ረገድ ኮሚሽነሩን ያግዛል፤
  ፭· ምክትል ኮሚሽነሩ የቦርዱ ፀሐፊ ነው።
  ፮· በአጠቃላይ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተካተቱት አላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ እንቅስቃሴዎች በኮሚሽኑ መዋቅር መሠረት የሚሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ይፈፅማል።
፲፰· በወረዳና በግድብ የሚገኙ የኮሚሽኑ አካላት ስለማቋቋም
በወረዳና በግድብ የሚገኙ የኮሚሽኑ አባላት ስለማቋቋም ስልጣንና ተግባር በመመሪያ ይወሰናል።

ክፍል ሦስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፱· የአሠራር ወጥነትን ስለማረጋገጥ
የኮሚሽኑ የአሠራር ወጥነት ለማረጋገጥ የሥራ አፈፃፀም መመሪያው የኮሚሽኑን አጠቃላይ ተግባራትና እንቅስቃሴዎች የሚገዛ ይሆናል።
፳· የበጀት ምንጭ
ለኮሚሽኑ ሥራዎች ማስፈፀሚያ የሚሆን በጀት ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ።
  ፩· በመንግሥት ከሚመደቡ በጀት
  ፪· ከሀገር ውስጥና አገር ውጭ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ፣ ማኅበረሰብ እና ግለሰቦች በእርዳታ በቦርድና በመዋጮ የሚገኝ ገንዘብ እና ማቴሪያል፤
  ፫· ከክልሉ ወረዳዎች፣ ከክልሎች ፣ ከፌዴራሉ መንግሥትና ከለጋሽ ድርጅቶች የሚሰጡ መመሪያዎች ፣ ዕቃዎችና የመሣሰሉት ለኮሚሽኑ ተጨማሪ ገቢዎች ሊሆኑ ይችላሉ።
  ፬· በጀቱ የገንዘብ መዋጮዎች ከተደረጉበት የብድርና ዕርዳታ ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ ተግባራዊ ይሆናል።

6. *The accountability of the commission shall be to the Regional Executive Committee and to the President;*
7. *Distributes the activities of the Commission through the Region;*
8. *Submits to the Board recommendations after inspecting related projects presented by applicants;*
9. *Delegates its powers to the Commission's Woreda's Council where it finds it necessary efficiently perform the activities of the Commission in the Regions;*
10. *diburses payments in accordance with the budget appropriated for the Commisssion Office of the Region;*
11. *Employs and administers the workers of the Commission in accordance with the appropriate law;*
12. *Without pregudice to the directives issued by the board and Executive Committee, the Commissioner shall be responsible to ensure that the activities of he Commission are appropriately being put into effect present to the execution process of he Commission;*
13. *Executes the powers and duties attributed to the Commission under Article of this Proclamation:*
17. *Deputy Commissioner*
   1. The Commission shall have one Deputy Commissioner
   2. The Deputy shall take charge to the absence of the commissioner;
   3. Deputy is accountable to the Commissioner;
   4. Aids the commissioner in executing the duties charged upon under Article 16 of the Proclamation;
   5. The deputy Commissioner is the securing of he Board;
   6. Executives the powers and duties given persuant to the structure of the commission in order to put into effect all the goals included in this Proclamation.
18. *Establishment of the Bodies of the commission Found in Woredas and Reservoirs*
   The establishment, powers and duties of the bodies of the commission found in Woredas and reservoirs shall be defined by directives.

PART THREE
MISCELLANEOUS PROVISIONS

19. *Ensuring the Uniformity of Execution*
   In order to ensure the uniformity of the performance of the Commission the job Execution directive shall govern the general duties and activities of the commission.
20. *Budget Sources*
   The budget sources for the execution of the works of the Commission shall be the following
   1. Budget appropriated by the government
   2. Domestic and foreign non-governmental organization the people, individuals, aid, loans, contribution funds and materials;
   3. Materials, equipment etc., given to the Commission from Woredas of the Region, Regions, Federal Government and philantropic organizations may be extra incomes to the Commission;
   4. The budget shall be put into effect pursuant to the loan and aid agreements made for the raising of funds.

፳፩· <u>ኦዲት</u>

፩· የኮሚሽኑ የሂሳብ መዝገቦችና ገንዘብ ነክ ጉዳዮች

ሀ) የኮሚሽኑ የሂሳብ መዝገቦችና ገንዘብ ነክ ጉዳዮች በኮሚሽኑ የውስጥ ኦዲተር በየጊዜው ይመረ ምራል፣

ለ) የኮሚሽኑ የሂሳብ መዝገቦችና ገንዘብ ነክ ጉዳዮች ቦርዱ በሚሠይመው ብቃት ያለው የውጭ ኦዲተር ይመረምራል፣

፪· የክልሉ መንግሥት ኦዲተር በማንኛውም ጊዜ የኮሚሽኑ የመንግሥታዊ በጀት አጠቃቀም ሊመረምር ይችላል።

፳፪· <u>የባንክ ሂሳብ</u>

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 ቁጥር 1 እና 2 የተጠቀሰው መዋጮ በኮሚሽኑ ሥም በባንክ ተቀማጭ ይሆናል።

፪· ኮሚሽኑ የሚከተሉት የባንክ ሂሳቦች ይኖሩታል።

ሀ· የውጭ ምንዛሬ ሂሳብ ፣ ከውጭ ዕርዳታና ብድር ሰጪዎች ለሚገኘው ገንዘብ

ለ· የብር/ የአገር ውስጥ ገንዘብ/ ሂባራ

፫· የኮሚሽኑ የባንክ ሂሳብ በኮሚሽነሩ እና የኮሚሽኑ የፋይናንስ መመሪያ ኃላፊ በአንድነት ይንቀሣቀሣል።

፳፫· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

እስማኤል አሊ ሲሮ
የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ርዕሰ መስተዳድር

21. *Audit*

1. The accounts and finance related affairs of the Commission
   a) shall, from time to time, be audited by internal auditors;
   b) shall be audited by a qualified external auditor appointed by the Board.
2. The auditor of the Regional Government may, at any time, audit the utilization of the governmental funds of the Commission.

22. *Bank Accounts*

1. The contribution made under sub-Articles(1) and (2) of Article 20 of this Proclamation shall be deposited in a bank in the name of the Commission;
2. The commission shall have the following accounts:
   a) foreign exchange account; for funds obtained from foreign aid and loans;
   b) Birr (Domestic money) Accounts.
3. The bank accounts of the Commission shall jointly be operated by the Commissioner and Head of the Commissions Finance Department.

23. *Effective Date*

This Proclamation shall be made effective as of the date of its print on the Afar National Regional Government Negarit Gazetta.

Ismael Ali Sierro
President of the Afar
National Regional State

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ
AFAR REGION NEGARIT GAZETA

AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር
አይሳኢታ – ሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፺፩

በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No.
AYSAITA – 8th July, 1999

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ
አዋጅ .... ገጽ ፩

CONTENTS

Proclamation No. 9/1999
A Proclamation to Establish the National Regional Government Council for the Administration of Judges .... Page 1

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፺ ዓ.ም. ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በአፋር ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት በአንቀጽ ፵፯/፪–፪ መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ ፤

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፱/፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ ፤

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፺ ዓ.ም. አንቀጽ "፬" ንዑስ አንቀጽ "፩" ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ "፩" ተተክቷል ።

"፬" የጉባኤው አባላት ፤

፩· በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፷፮/፩ መሠረት ጉባኤው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል ።

ሀ)	የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት	ሰብሳቢ
ለ)	ከክልሉ መንግሥት ም/ቤት ሶስት	አባል
ሐ)	ከጠቅላይ ፍ/ቤት በሥራ ቀደምትነት ያላቸው ሁለት ዳኞች	አባል
መ)	ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ሶስት ዳኞች	አባል
ሠ)	ከወረዳ ፍ/ቤቶች ሁለት ዳኞች	አባል

፫· አዋጁ የሚፀናበት ፤

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

እስማኤል አሊ ሲሮ

የአፋር ብመክ/መንግሥት
ርዕሰ መስተዳድር

PROCLAMATION PROVIDED TO AMEND THE PROCLAMATION TO ESTABLISH THE ADMINISTRATIVE COUNCIL OF JUDGES OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

WHEREAS, it is deemed necessary to amend the Afar National Regional State Proclamation to Establish the Council for the Administration of Judges No. 9/1999;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 47(2) of the constitution of the Afar National regional Government, it is hereby proclaimed as follows,

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "Proclamation to Amend the Proclamation to Establish the National Regional Government Council for the Administration of Judges No. 9/1999

2. *Amendment*

   The Afar National Regional State Proclamation to Establish the Council for the Administration of Judges No. 4/1998 Article 4 and sub-Article (1) is hereby deleted and replaced by the following new sub-Article (1):

   "4. *Members of The Council*

   In accordance with Article 66(1) of the Regional Constitution, the Council shall have the following members:

a)	President of the Supreme Court	Chairperson
b)	Three members of the Council of the Regional Government	Member
c)	Two Senior Judges of the Supreme court	Member
d)	Three Judges of the High Court	Member
e)	Two Judges of the Woreda Court	Member

7. *Effective Date*

   This Proclamation shall come into force as of its publication in the Negarit Gazette.

Ismail Ali Sero

President of the Afar National
Regional State

ያንዱ ዋጋ 3:30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

QAFAR XOLETIH RAKAKAYA

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ
AFAR REGION NEGARIT GAZETA

AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፯
አይሳኢታ – ፲፱፻፺፫

በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 7
AYSAITA 2001

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፫ ዓ.ም.
"የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ —" .... ገጽ ፩

CONTENTS

Proclamation No. 10/2001
''Establishment of the Office of the Auditor General of the National Regional State of Afar Proclamation ...'' .... Page 1

አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፫ ዓ.ም

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር የክልሉን ኢኮኖሚ በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ በማግኘት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን፤

በልዩ ልዩ የልማትና አስተዳደር መስኮች የተሰማሩ የክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ድርጅቶችና ማኅበራት የገንዘብ አስተ ዳደር ተገቢውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት የተከተለ የገቢ አሰባሰባቸው የወጪ አፈ.ቃቀዳቸውና የንብረት አስተዳደራቸው የመንግሥትን ሕግና መመሪያ ተከትሎ የተፈፀመ መሆኑን ዕቅድና ፕሮግራማቸ ውንም በቅልጥፍና እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በማከናወን የሚጠበቅባቸውን ግብ ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በክልሉ መንግሥት አወቃቀር በየደረጃው ክልላዊ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች ሊኖር የሚገባውን ተጠያቂነት በማረጋገጥ የዲሞክራሲን ሥርዓት ለማስፈን ኦዲት ዓይነተኛ መሣሪያ በመሆኑ፤

የሀገሪቱን መንግሥት አዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲን በሚገባ ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንድ በክልላዊ መንግሥት ይዞታ ሥር የሚገኙ የአስተዳደር የልማትና የአገልግሎት ተቋማትን ብቃት ለመቆጣጠር በተጠናከረና ዘመናዊ በሆነ የኦዲት ተግባር መታገዝ ያለበት በመሆኑ፤

ለዚህ ተግባራዊነት የክልሉን ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ማቋቋም በማስፈለጉ፤ በክልሉ ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፵፱ ንዑስ አንቀጽ ፫ ተራ ቁጥር ፫.፮ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፤

PROCLAMATION No. 10/2001
PROCLAMATION TO ESTABLISH THE OFFICE OF THE AUDITOR GENERAL OF THE NATIONAL REGIONAL STATE OF AFAR

WHEREAS the strengthening of the audit system contributes a lot in providing reliable information necessary to properly direct and administer the regional econony:

WHEREAS, it has become necessary to ensure that the financial management of the Regional Government offices, organizations and associations engaged in various developmental and administrative activities follows proper accounting systems; that the manner of their revenue collection, fund disburesement, and porperty management is in accordance with the Government law and directives; and that they carry out their plan and programmes efficiently and economically so as to achieve their objectives;

WHREAS, audit is the proper means to ensure responsibilities of the Government offices and organizations in the Region in order to guarantee a democratic order;

WHEREAS, it is necessary that the administrative, developmental, and service rendering institutions under the Regional government be supported by a modern and reliable audit system in order to regulate their efficiency, and to properly implement the New Economic Policy of the Country;

WHEREAS, in order to attain the foregoing objectives, it is necessary to establish the Regional Office of the Auditor General;

NOW– THEREFORE, in accordance with Sub–article 3(3.6) of Article 49 of the Constitution of the Regional Government, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፳፪
Negarit G.P.O.Box 22

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌ

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር…፲፱፻፺፫··ዓ·ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· **ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩· "የመንግሥት መሥሪያ ቤት" ማለት በክልሉ መንግሥት የተቋቋመ ቢሮ፣ ኮሚሽን፣ ባለሥልጣን፣ ጽ/ቤት፣ ተቋም፣ ኤጀንሲ ወይም ማናቸውም ሌላ የክልሉ መንግሥት መ/ቤት ነው።

፪· "ድርጅት" ማለት በክልሉ መንግሥት የተቋቋመና በሙሉ ወይም በከፊል የክልሉ መንግሥት የሆነ የማምረቻ የማከፋፈያ አገልግሎት ሰጭ ወይም ሌላ የንግድ ድርጅት ነው።

፫· "ማኅበር" ማለት በክልሉ መንግሥት የተቋቋመ ማኅበር የገበሬ ማኅበር፣ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበር እና ሌሎች ሕዝባዊ ድርጅቶች ናቸው።

፫· **መቋቋም፣**

፩· በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፵፱ ንዑስ አንቀጽ ፫ ተራ ቁጥር ፫.፮ መሠረት ከዚህ በኋላ "የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ሠመራ ሆኖ ለሥራው አስፈላጊ በሆነ ቦታ ሁሉ ቅርንጫፍ ቤቶች ይኖሩታል።

፬· **የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ድርጅታዊ መዋቅር፣**

የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት አንድ ዋና ኦዲተር፣ መምሪያ ኃላፊዎች፣ ኦዲተሮችና ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል።

፭· **የመሥሪያ ቤቱ ዓላማ፣**

፩· የክልሉን መንግሥት ዕቅድ በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣

፪· የክልሉን መንግሥት ገንዘብና ንብረት በፌዴራል መንግ ሥትና በክልሉ ምክር ቤት በወጡት ሕጎችና ደንቦች መሠረት መሰብሰቡን መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥና የደረሰበትን ውጤት ለክልሉ ምክር ቤት ሪፖርት ማቅረብ፣

፫· በክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የፋይና ንስና የክዋኔ ኦዲት ማካሔድ፣

፬· አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሣብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣

፭· በሂሣብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩት ለክልሉ መንግሥት ሠራተኞች ድርጅቶች ሙያዊ እገዛና ምክር መስጠት፣

፮· የክልሉ መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሂሣብ የሚመ ረመርበትን የኦዲት ደረጃ (እስታንዳርድ) ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

፯· በክልሉ ሐብትና ንብረት ላይ የእምነት ማጉደል ወንጀሎች ተፈጽመው ሲገኙ ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው አስተያየት መስጠትና የመሥሪያ ቤቱን የሂሣብ አያያዝ የገንዘብ የንብረት አስተዳደር የሚጠናከርበትን ተገቢ አስተያየትና ምክር መስጠት፣

PART ONE
General Provisions

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Establishment of the Office of the Auditor General of the National Regional State of Afar Proclamation No. /2001."

2. *Definitions*

In this Proclamation:

1) "Government Office" means bureau, commission, authority office, institution, agency, or any other office established by the Regional Government.
2) "Organization" means any production, distri bution, service rendering or any other trading organizations established, and owned wholly or partially, by the Regional Government.
3) "Association" means the Cooperatives, Peasant Associations, Urban Dwellers Associations, and other civic organizations established by the Regional Government.

3. *Establishment*

1) The Office of the Auditor General (hereinafter referred to as the "Office of the Auditor General of the National Regional State of Afar") pursuant to Sub–Article 3(3.6) of Article 49 of the Constitution of the National Regional State of Afar, is hereby established as an autonomous office.
2) The Office of the Auditor General of the National Regional State of Afar shall be in Semera, and it shall have branch offices elsewhere as may be necessary.

4. *Organizational Structure*

The Office of the Auditor General shall have an Auditor General, the department heads, auditors, and other personnel.

5. *Objectives*

1) To strengthen the audit system with a view to providing reliable information necessary to properly direct and administer the plans and budget of the Regional Government;
2) To ensure that the revenue and property of the Regional Government are collected, managed, and properly used in accordance with the laws and regulations of the Federal Government and the Regional Council, and submit the reports of the findings to the Council;
3) To carry out audits on financial operations and accomplishment of the Regional Government offices and orgnaizations;
4) To make efforts in cooperation with the appropriate organs with a veiw to enhancing and strengthening the accounting and audit professions.
5) To provide professional support and advice for the employees of the Government and orgnaizations engaged in accounting and audit professions;
6) To issue audit standard for auditing the accounts of the Government offices and organizations; and follow up the implementation of same;
7) To submit its recommendations on the appropriate legal measures to be taken where there is breach of trust on the Region's resources and properties; and forward appropriate suggestions and advice as to how the accounting, finance, and property administration of the Office be strengthened.

፮· ስለ ዋና ኦዲተር አሿሿምና፣ ተጠሪነት፣

፩· ዋና ኦዲተር በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማል።

፪· ዋና ኦዲተር ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ይሆናል። የክልሉ ምክር ቤት በማይሰበሰብበት ጊዜ ተጠሪነቱ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል።

ክፍል ሁለት
የክልሉ የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ሥልጣንና ተግባር

፯· የክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ሥልጣንና ተግባር፣

የክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በሕግ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን የሚያስፈልገው ሥልጣን ሁሉ ይኖረዋል ። በዚህ አጠቃላይ አነጋገር ሳይወሰን የክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት፣

፩· የክልሉ ምክር ቤት ጽ/ቤትን ጨምሮ የክልሉን መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ድርጅቶችና ማኅበራት ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል።

፪· የክልሉ መንግሥት ከብር ፪፻፶ሺ (ከሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ) በላይ የሚጠይቅ ሥራ ለግል ተቋራጮች እንዲሰሩ በውል የሰጠ እንደሆነ ይህንኑ የመንግሥት ነክ የሆነ የግል ሥራ ተቋራጮች ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል።

፫· ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀው ሆኖ ወንጀል ለመፈጸሙ በቂ ፍንጭ ያገኘ እንደሆነ ሥራው የሚጠይቀው ገንዘብ ከብር ፪፻፶ሺ (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ) በታች ቢሆንም የመንግሥት ሥራ ነክ የሆነውን የተቋራጮችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል።

፬· በዚህ አንቀጽ (፩) (፪) እና (፫) በተመለከተው መሠረት ያከናወነው የምርመራ ውጤት እንደነገሩ ሁኔታ ለክልሉ መንግሥት ምክር ቤት ፣ መሥሪያ ቤት ፣ ለድርጅቱ እና ለማኅበራቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል ። የክልሉ ዋና ኦዲተር የምርመራው ውጤት ወንጀል መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ከሆነ ወዲያውኑ ለክልሉ ምክር ቤት ሪፖርት ያደርጋል።

፭· ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሳብና የንብረት ምርመራ ሥርዓትና ደረጃን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ያወጣል።

፮· ማናቸውም የክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል።

፯· አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማናቸውም የክልሉ መሥሪያ ቤት የውስጥ ኦዲተሮች የመሥሪያ ቤታቸውን ሂሳብና ንብረት በመመርመር ውጤቱን እንዲገለጹለት ሊያደርግ ይችላል።

፰· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንደአስፈላጊነቱ ለውስጥ ኦዲተሮች ሥልጠና ይሰጣል።

፱· አንድ ሂሳብ ወንጀል ባለበት ሁኔታና ታማኝነት በጎደለው አኳኋን መያዙን ለማመን ምክንያት ያለው እንደሆነ ይህንን ሂሳብ በሚመለከቱ ካዝናዎች ፣ መጽሐፎች ፣ መዝክሮች ፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና በሌሎች መረጃዎች እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መዛግብቱ የሚገኙበትን ክፍል የንብረት ክፍሉንና ቤቱን ያሽጋል።

፲· የፋይናንስ ቢሮ ስለ ገንዘብና የሂሳብ አጠባበቅ በሚያዘጋጀው ደንብ ላይ አስፈላጊውን ምክር ይሰጣል።

6. *Appointment and Accountability of the Auditor General*

1) The Auditor General shall, upon recommendation of the Head of the Administration, be appointed by the Regional Council.
2) The Auditor General shall be accountable to the Regional Council and, between sessions, he sahll be accountable to the Head of the Administration.

PART TWO
Powers and Functions of the Office of the Auditor General of the Region

7. *Powers and Functions of the Office of the Auditor General*

The Regional Office of the Auditor General shall have all the powers necessary for carrying out functions assigned to it by law. Without limiting to the generality of the aforementioned, the Regional Office of the Auditor General shall:

1) audit and cause to be audited the accounts of the Regional Government offices, organizations, associations, including the accounts of the Regional Council;
2) audit the accounts of private contractors relating to the Government contractual work which involves a sum exceeding Birr 250,000 (Birr two hundred fifty thousands);
3) Without prejudice to Sub-Article 2 of this Article, audit the accounts relating to the Government contractual work not withstanding that the sum involved does not exceed Birr 250,000 (Birr two hundred fifty thousand) where it has sufficient indication of the commission of a crime;
4) notify to the Head of an audited government office, organization, and associations, as the case may be, the result of the audits carried out in accordance with Sub-Articles (1), (2) and (3) of this Article; and the Auditor General of the Region shall, where the result of the audits ascertains the commision of a crime, report such case immediately to the Regional Council;
5) issue, in cooperation with other concerned offices, directives concerning accounts and property auditing procedures and standards;
6) issue certificates of competence to internal auditors who may be employed by any Regional Government office and organization;
7) where it deems necessary, it may instruct internal auditors of any Regional office to audit the accounts and properties of their respective offices, and submit the results to it;
8) train, as it may be necessary, internal auditors in cooperation with the concerned organs;
9) where it has reasons to believe that any account has been kept in a criminal and dishonest manner, impounded such cases, books documents, ledgers, vouchers and other materials relating to such accounts as well as, where it finds it necessary, a room, a storeroom, and a storehouse wherein the books of accounts are kept;
10) give the necessary advice on the finanicial and accounting regulations to be prepared by the Finance Bureau;

፲፩. ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልሉና የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል። የክልሉ መንግሥት የኦዲትና የሂሳብ ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል ።

፲፪. ከፌደራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት እና ከሌሎች ክልል ኦዲት መሥሪያ ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል ።

፲፫. በክልሉ ውስጥ በግል የሚሠሩ ኦዲተሮችና የሂሳብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለመሰማራት መቻላቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ይሰጣል ፣ ያድሳል ፣ ያግዳል ፣ ይሰርዛል ፣ ስለምሥክር ወረቀት አሰጣጥ እድሳትና ስለአገልግሎት ዋጋ ክፍያ ዝርዝሩ የክልሉ የሥራ አስፈፃሚ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል ።

ክፍል ሦስት
የዋና ኦዲተር ሥልጣንና ተግባር ፣

፰. የዋና ኦዲተር ሥልጣንና ተግባር፤

ዋናው ኦዲተር የዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በመሆን በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፯ ለዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

፩. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) (፪) እና (፫) መሠረት ስለሚከናወነው ምርመራና አጠቃላይ ዓመታዊ ሪፖርቱን ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል።

፪. የፋይናንስ ቢሮ የክልሉ መንግሥት ያለፈውን በጀት ዓመት ገቢና ወጭ ሀብትና ዕዳ እንዲሁም የመንግሥት ገንዘብ ነክ የሆኑ መረጃዎችን ሂሳብ የበጀት ዓመቱ እንደተጠናቀቀ በተቻለ ፍጥነት ዘግቶ ለምርመራ ለክልሉ ዋና ኦዲተር ይላካል ፣ የክልሉ ዋና ኦዲተርም የሂሳብ ዘገባው እንደደረሰው በአራት ወር ጊዜ ውስጥ መርምሮ ፣ አጥንቶ ሪፖርቱን ከእነ አስተያየቱ ለቢሮው ይልካል ። ለክልሉ ምክር ቤት በሚያቀርበው ዓመታዊ ዘገባ ውስጥ ሪፖርቱ እንዲካተት ያደርጋል።

፫. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ውጤቱን እንዲያውቁ የተደረጉት አካላት የሰጡት አስተያየትና ያቀረቡት ተቃውሞ አጥጋቢ ያለመሆኑን የገመተ እንደሆነ ይህን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሰው ዘገባ ውስጥ ያስገባል ።

፬. ተግባሩን በሚገባ ለማከናወን መሥሪያ ቤቱን ያደራጃል፣ ይመራል ፣ ያስተባብራል።

፭. በክልሉ ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፺፮ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የመሥሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያጸድቃል ። ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

፮. በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ሕግና ደንብ ውስጥ የተመለከቱትን መሠረታዊ ዓላማዎችን ጠብቆ የክልሉ ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ለመሥሪያ ቤቱ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ይቀጥራል ያስተዳድራል።

፯. ለሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቂ መመሪያ በመስጠት የኦዲት ምርመራ እንደአግባቡ በግል ኦዲተሮች ወይም በሌሎች ባለሙያዎች እንዲከናወን ይወከላል ። ሥራቸውንም ይከታተላል።

፰. በክልሉ ሀብትና ንብረት ላይ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን በማናቸውም ጊዜ ኦዲት ያደርጋል። በቂ ምክንያት ሲኖረው የተጀመረውን ምርመራ ለማቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ ለማድረግ ይችላል ።

11) make, in cooperation with other concerned Regional and Federal Government offices, efforts with a view to promoting the accounting and audit professions; and conduct the necessary supervison so that the Regional Government's audit and acconting professions be developed in the correct course;

12) establsish close relations and cooperation with the Federal Office of the Auditor General and other Regional Offices of the Auditor General in respect of designing ways and means for enhancing the auditing;

13) issue, renew, suspend, and revoke certificates of competence of private auditors and accountants in the Region; particulars of the issuance and renewal of such certificates, and service charges for same shall be determined by the regulations to be issued by the Executive Committee of the Region.

PART THREE
Powers and Functions of THE Auditor General

8. *Powers and Functins of the Auditor General*

The Auditor General is the Head of the Office of the Auditor General, and shall have all the powers and functions assigned to the Office of the Auditor General under Article 7 herein.

1) He shall submit a consolidated annual report on auditing carried out in accordance with Sub-Article (1), (2) and (3) of Article 7 herein, and on the activities of the Office of the Auditor General to the Council of the Region.

2 He shall review the annual report which the Regional Finance Bureau submits to it concerning the Regional Government receipts and expenditures, assets and liabilities as well as the financial statistical data within four months of receipt, and submit his comments thereon to the Bureau; include same in his annual report to be submitted to the Council of the Region.

3) He shall include the views and objections forwarded by the organs notified the findings of the audits pursuant to Sub-Article (4) of Article 7 of this Proclamation in the report mentioned in Sub-Article (1) of this Article, where he deems such views and objections are unsatisfactory.

4) He shall organize, direct, and coordinate his office in order to properly accomplish his duties.

5) He shall, accordance with Sub-Article (3) of Article 96 of the Constitution of the Regional Government, directly submit his office's budget for approval to the Council, and implement same upon approval.

6) He shall employ all necessary personnel for the Office, and administer same in accordance with regulations to be issued by the Regional Council in conformity with the basic objectives stated in the law and regulations of the Regional Civil Service.

7) Where it is necessary, he shall give appropriate instruction to, and delegate, the private auditors or other professionals, as the case may be, to carry out audits; and follow up their activities.

8) Where he believes that there is commission of a crime against the Region's resources and properties, he shall carry out audits at any time; and he may discontinue audits, or conduct further audits on a sufficient cause.

ክፍል አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፱. በጀትና ሂሳብ ምርመራ፣

፩. ለዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከተፈቀደው በጀት ውስጥ የ፫ (ሦስት) ወር ድርሻ የሆነውን የሥራ ማስኬጃ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ሥም በተከፈተው ሂሳብ ውስጥ በአንድ ጊዜ በቅድሚያ እንዲቀመጥ ያደርጋል ።

፪. የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ሂሳብ በክልሉ ምክር ቤት፣ ምክር ቤቱ በማይሰበሰብበት ጊዜ በክልሉ ምክር ቤት ርዕሰ መስተዳድር በሚሰየም አካል ይመረመራል።

፲. ስለ ኦዲት ሥርዓት የጊዜ ገደብ፤

፩. የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት አንድ ሂሳብ ኦዲት ሲያደርግ ለጉዳዩ አስፈላጊ እንደመሰለው አንድ በአንድ በዝርዝር ወይም በአልፎ አልፎ የኦዲት ዘዴ ሊመረመር ይችላል ። ቢሆንም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት ሂሳቦችን መርምሮ በሚያቀርበው ዘገባ ውስጥ ለእያንዳንዱ ሂሳብ ያመራመሩን ጥልቀት መግለጽ አለበት ።

፪ የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በሚያከናውናቸው ምርመራዎች ሁሉ ከሚመረመረው የበጀት ዓመት ወደኋላ ከሁለት የበጀት ዓመታት ማለፍ የለበትም ። ነገር ግን በእርሱ ግምት ወንጀል መፈጸሙን ያመነ እንደሆነ ከተባሉት ሁለት የበጀት ዓመታት ወደኋላ አልፎ ሊመረመር ይችላል።

፲፩. የተመርማሪዎች ግዴታ፣

፩. የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኦዲተሮች ወይም የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ወኪሎች ለምርመራ ጠቃሚና አስፈላጊ የሚመስሏቸውን መጻሕፍት ፣ መዝክሮች ፣ መዝገቦች ፣ ሰነዶችና ሌሎች የጽሁፍና የቃል መረጃዎች ሁሉ ሲጠይቁ የተጠየቀውን ግለሰብ ፣ ሠራተኛ ወይም ባለሥልጣን በትክክልና በተሟላ አኳኋን ወዲያውኑ የማቅረብ ግዴታ አለበት ።

፪. የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት እንዲቆጣጠራቸው በዚህ አዋጅ ሥልጣን የተሰጠው አካላትን ገንዘብ ወይም ንብረት የተረከበ ወጪ ያደረገ የከፈለ ወይም የሂሳብ ኃላፊ የሆነ ማንኛውም ሰው ሲጠየቅ ሂሳቡን ኦዲት የማስደረግ ግዴታ አለበት።

፫. ተመርማሪው መሥሪያ ቤቶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በተላኩ ሪፖርቶች በተገለጸ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት ዕርምጃ እንዲወስዱ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦችና አስተያየት መሠረት ከ፴ (ሠላሳ) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ዕርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው ። እርምጃ ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው።

፬. የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ለክልሉ ምክር ቤት በሚያቀርበው ሪፖርት ውስጥ ድክመት የታየባቸው መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች በታዩት ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ወስደው ይህንኑ ለምክር ቤቱና ለዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።

፭. ተመርማሪው መሥሪያ ቤት ለኦዲተሮች ሥራ የሚሆን ቢሮ የመስጠት ግዴታ አለበት ።

PART FOUR
Miscellaneous Provisions

9. *Budget and Auditing*

1) A proportionate quarterly appropriations of the operational budget of the approved budget of the Office of the Auditor General shall be deposited in advance in the Commercial Bank of Ethiopia in account opened in the name of the Office of the Auditor General of the Region.

2) The accounts of the Office of the Auditor General shall be audited by an organ to be designated by the Regional Council and, between sessions, by the Head of the regional Council.

10. *Audit Procedures and Period of Limitation*

1) The Office of the General Auditor may audit accounts in detail or by a system of spot-checking, whichever it deems it appropriate in a given case; provided however, that any report that it submits in accordance with sub-Article (1) and (2) of Article 8 herein concerning the findings of audits of the accounts, shall contain descriptions of the nature and extent of the audits carried out with respect to each account.

2) The Office of the Auditor General shall not carry out audits covering a period earlier than two fiscal years prior to the fiscal year in respect of which the audit is to be carried out unless he believes that a crime has been committed during the period earlier than two fiscal years.

11. *Duties of those to be Audited*

1) Any individual, employee, or an official, upon request by the auditors of the Office of the Auditor General or representatives of the Office of the Auditor General, shall, forthwith make available accurate and complete books, documents, ledgers, vouchers and all other documentary or oral evidence which the auditors of the Office of the Auditor General or the representatives of same deem it useful and necessary for auditing.

2) Any person who has had in his custody or has paid or has expended or is in charge of the accounts of the money and property of the organs auditable under the provisions of this Proclamation, shall upon request, have the duty to have his accounts audited.

3) Aduitee Government offices have the duty to take corrective measures, within 30 days from the date of receipt of the reports, on recommendations and comments based on audit findings and included in the audit reports sent to them by the Office of the Auditor General; and if they fail to take such measures, they shall have to notify same and the reasons thereon to the Office of the Auditor General within the period mentioned herein.

4) The Head of any audited office whose weaknesses were commented in the report of the Office of the Auditor General submitted to the Council of the Region, shall have the duty to take appropriate remedial measures and inform same to the Council and the Office of the Auditor General.

5) Auditable Government offices have the duty to provide an office appropriate for auditing.

፲፪· <u>የማሳወቅ ግዴታ፤</u>

ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኦዲት ሲያከናውን በጉዳዩ ላይ ወንጀል መሠራቱን ያመነ እንደሆነ ይህንኑ ለፍትህ ቢሮ እና ለሚመለከተው ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት የበላይ ኃላፊ ማስታወቅ አለበት ፤

፲፫· <u>ተጠያቂ፡</u>

ያለበቂ ምክንያት በክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በቀረቡ ኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችና ሃሳቦች ላይ በወቅቱ እርምጃ ያልወሰደ ወይም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት መፈጸም ሲኖርበት ለመፈጸም ፈቃደኛ ሆኖ ያልተገኘ ማንኛውም ሰው በዲሲፕሊን ወይም እንደአስፈላጊነቱ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል።

፲፬· <u>ቅጣት፤</u>

ማንኛውም ሰው፤

፩· የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በቀጥታ ወይም በኦዲተሮች ወይም በወኪሎቹ አማካይነት ለምርመራ እንዲቀርብ ብሎ የሚጠይቀውን መጻሕፍት መዘክሮች መዛግብት ሰነዶችና ሌሎች የጽሁፍ ወይም የቃል መረጃዎች ያላቀረበ ወይም፤

፪· ለዋና ኦዲተር ወይም ለወኪሎች ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ ወይም እውነተኛ መሆኑን ለማመን ምክንያት ሳይኖረው ማናቸውም መረጃ የሰጠ ወይም፤

፫· የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ሥራ በሚገባ እንዳይከናወን ያሰናከለ፤ እንደሆነ እስከ ሁለት (ሁለት) ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም ሁለት ሺ ብር (፪ሺ) የገንዘብ መቀጫ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

፲፭· ቀደም ሲል የክልሉን ሴክተር መ/ቤቶች ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮/፲፱፻፺፩ አንቀጽ ፲ የክልሉን ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ በዚህ አዋጅ ተተክቷል ።

፲፮· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ፤</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

ሠመራ ________ ቀን ፲፱፻፺፫_______

እስማኤል አሊ ሴሮ
የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት ምክር ቤት
ርዕሰ መስተዳድር

12. *Duty to Notify*

The Office of the Auditor General shall have a duty to notify to the Justice Bureau and the Head of the office or the organization concerned, where in the course of its auditing, it believes that a crime has been committed.

13. *Accountability*

Any person who fails to take measures without good cause within 30 days from the date of receipt of the reports, on recommendations and comments included in the audit reports of the Regional Office of the Auditor General; or fails to comply with the provisions of this Proclamation when he is required to do so, shall be administratively or, as may be necessary, criminally liable.

14. *Penalty*

Any person who:

1) fails to produce or make available books, documents, ledgers, vouchers or other documentary or oral evidence which the Office of the Auditor General directly or through its auditors or its representatives requires for auditing;
2) gives to the Auditor General or the representative any information which is false or which he has no reason to believe to be true;
3) Obstructs the proper carrying out of the functions of the Office of the Auditor General; shall be punished with imprisonment not exceeding two years, or with a fine not exceeding birr two thousand (Birr 2000), or with both such fine and imprisonment.

15. Provisions relating to the powers and duties of the Regional Office of the Auditor General, under the Definition of Powers and Duties of the Sector Offices of the Regional Government Proclamation No./6/1991 Article 10 is hereby repealed.

16. Effective Date

This Prolcamation shall enter into force on the date of its publication in the regional Negarit Gazeta.

Done at Semera, this —— day of ——, 2001

Ismael Ali Sero
Head of the Council of the National Regional
State of Afar

QAFAR XOLETIH RAKAKAYA

የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፪
ሠመራ – የካቲት ፱ ቀን ፲፱፻፺

በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1rd Year No. 2
SEMERA 16th February, 1998

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፺ ዓ·ም
"የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ .... ገጽ ፩

CONTENTS

Proclamation No. 2/1998
''Afar National Regional State's Negarit Gazeta Establishment Proclamation''.–................... Page 1

አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፺ ዓ·ም
የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ፤

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሕግ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለመወጣት የሚያስችሉ የራሱ ሕጐች በክልሉ ምክር ቤት ተመክረው የወጡና የሚወጡ በመሆኑ ፤

በክልሉ ምክር ቤት የወጡ የተለያዩ ሕጐች ኃይል ኖራቸው ፈጻሚ የሚሆኑት የሕጉ ተጠቃሚ የሆነው ሕዝብና የክልሉ መስተዳድር የሕግ አውጪ የሕግ ተርጓሚና የሕግ አስፈጻሚ አካላት በሕዝብ ጋዜጣ በቅድሚያ እንዲያውቁት ሲደረግ ስለሆነ ሕጐች የሚወጡበት ኦፊሴል ጋዜጣ ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ በንዑስ አንቀፅ ፪/፪ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

አንቀጽ ፩

፩· **አጭር ርዕስ**
ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ ፪

፪· **መቋቋም**
በዚህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ ተብሎ የሚጠራ የክልሉ መስተዳድር ጋዜጣ ተቋቁሟል።

AFAR NATIONAL REGIONAL STATE
NEGARIT GAZETA CONTENTS
Proclamation No. 2/1998
Afar National regional State Negarit Gazeta Establishment Proclamation........Page......

Proclamation No.2/1998
A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE AFRAR NATIONAL REGIONAL SATATE NEGARIT GAZETA

WHEREAS laws are enacted by the House of the People of the Afar National Regional State to enable the State to discharge the duties and responsibilities entrusted to it;

WHEREAS, it has bacame essential to establish the state's own Negarit Gazeta through which the regional population and its different executive, legislative and judiciary bodies are informed about these laws;

NOW– THEREFORE– in accordance with Article 47 (2.2) of the Constitutions of the Afar National Regional State, it is hereby proclaimed as follows:

Article One

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the ''Afar National Regional State Negarit Gazeta Establishment Proclamation NO.2/1998.

Article Two

2. *Establishment*
The Afar Regional administration's Negarit Gazeta, to be known as the Afar National Regional State Negarit Gazeta, is hereby established.

<u>አንቀጽ ፫</u>

<u>በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ የሚወጡ ጉዳዮች፤</u>

፩· የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ የሚወጡ ጉዳዮች ለክልሉ መስተዳድር የተለያዩ አካላት በክልሉ ሕገ መንግሥት በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት

ሀ) የክልሉን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች፤

ለ) ከፍተኛ የክልሉ ባለሥልጣኖችን ሹመት ሽረት የማዕረግ ስም ሽልማትና ኒሻን፤

ሐ) ለሕዝብ ጥቅም የላቸው የክልሉ ሕዝብ ማወቅ የሚገባቸው ማስታወቂያዎች ናቸው።

፪· በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ የሚወጡ ሕጐችም በክልሉ ሕገ መንግሥት ደንብ ለማውጣት ሥልጣን ባላቸው አካላት ከዚህ በላይ የተገለጹትን ጉዳዮችን ለሕዝብ ለማስታወቅ የሚወጡ አዋጆች፣ ድንጋጌዎች፣ ደንቦችና የሕግ ክፍል ማስታወቂያዎች ይሆናሉ።

<u>አንቀጽ ፬</u>

፫· <u>በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ ሕጐችን የማውጣት ስልጣን ያላቸው አካላት፤</u>

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ ሕጐችን ደንቦችን፣ አዋጆችን ድንጋጌዎችን የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ዎችን ማውጣት የሚችሉት ከዚህ በታች የተመለከቱት ናቸው።

ሀ) የክልሉ ምክር ቤት

ለ) የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣን ሲሰጠው የክልሉ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ናቸው።

፬· <u>የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ ነጋሪት ጋዜጣ ቅርፅ/ፎርም/</u>

ሕጋዊ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሠራ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግንሥት ነጋሪት ጋዜጣ የሚከተለው ቅርፅ (ፎርም) የሚያሟላ ነው።

፩· የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣው ተከታታይ ቁጥሮችን በመያዝ የክልሉን መስተዳድር አርማ ያለው ሆኖ የማዕከላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ ቅርፅ /ፎርም/ ይኖረዋል።

፪· በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣው ግርጌ የክልሉ መሰተዳድር ምክር ቤት ማኅተም ያረፈበት መሆን አለበት፤

<u>አንቀፅ ፭</u>

፭· <u>የሕጐች ተፈጻሚነት፤</u>

በዚህ አዋጅ በተቋቋመው በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ የሚወጡ አዋጆች ድንጋጌዎች ደንቦችና ሌሎች የሕግ ክፍል ማስታወቂያዎች በማንኛውም የክልሉ መስተዳድር አካላት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

<u>አንቀጽ ፮</u>

፮· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ፤</u>

ይህ አዋጅ በዚህ አዋጅ መሠረት በተቋቋመ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሰመራ የካቲት ፱ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም·
እስማኤል አሊ ሲሮ
የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት ርዕሰ
መስተዳድር

Article Three
Issues to be published in the Negarit Gazeta of the Afar National Regional State

1. Issues to be published in the Negarit Gazeta of the Afar National Regional State in accordance with the powers vested by the regional state's constitution in the regional state and its different bodies are:
   (a) Economic, social and administrative affairs of the region;
   (b) Promotion and demotion of senior officials of the regional state, titles, awards and oreders; and
   (c) Public notices regarded essential for public knowledge.
2. Proclamations, provisions, regulations and legal notices enacted and issued by the regional stae, legislative bodies in accordance with the regional constitution shall also be publihsed in this gazeta for public information.

Article Four

3. *Bodies authorized to publish law in the Afar Nationa Regional State Negarit Gazeta*
   Bodies who have the power to publish laws, proclamation, regulations, legal notices and provisions in the Afar National Regional State Negarit Gazeta are the following:
   (a) the House of the People of the Regional state;
   (b) the regional state's executive committee when authorized by the Region's House of the people.
4. Format of the Afar National Regional State
   The format of Afar Regional State Negarit Gazeta, established legally by this constitution, shall have the following format:
   1) The Afar National Regional State Negarit Gazeta, which bears consecutive issue numbers and the regional state's emblem, shall have the same format as that of the federal gazeta.
   2) The Afar National Regional State Negarit Gazeta shall bear the stamp of the Regional Administrative Council.

Article Five

5. All Proclamations, regulations, provisions and legal notices published in the Afar National Regional State Negarit Gazeta shall be implemented by the State's adminstrative bodies.

Article Six

6. *Effective Date*
   This Proclamation establishing the Afar National Regional State Negarit Gazeta shall enter into force as of the 16th day of February, 1998.

Semera, 16th 1998
Ismail ali Sero
President, Afar National
Regional State.

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፫
ሠመራ – የካቲት ፱ ቀን ፲፱፻፺

በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1st Year No. 3
SEMERA 16th February, 1998

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫/፲፱፻፺ ዓ.ም
"የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋሚያ የወጣ አዋጅ .... ገጽ ፩

CONTENTS

Proclamation No. 3/1998
''Afar National Regional State's Courts Establishment Proclamation''.. .... Page 1

አዋጅ ቁጥር ፫/፲፱፻፺
የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዳኝነት ሥልጣን በፌዴራል መንግሥቱና በክልሎች የተከፋፈለ በመሆኑ፣

የክልሉን ሕገ መንግሥት መሠረት በማድረግ የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት ፍርድ ቤቶችን ሥልጣን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ (፪.፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ
ይህ አዋጅ "የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፫/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ
በዚህ አዋጅ ውስጥ፣
፩. "የክልል መንግሥት" ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው።
፪. "የክልሉ መንግሥት ባለሥልጣኖች" ማለት የክልሉ መንግሥት ም/ቤት አባላት፣ የክልሉ ቢሮ ኃላፊዎች የክልል መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞችና በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የክልሉ መንግሥት ባለሥልጣኖች ናቸው።
፫. "ፍርድ ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋሙ የክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ወረዳ ፍርድ ቤት ናቸው።

Proclamation No. 3, 1998
Afar National Regional State Courts Establishing Proclamation

WHEREAS, in the Federal Democratic Republic of Ethiopia, judicial power is vested in both the Federal Government and the Regional States;

WHEREAS, it is found necessary to determine the jurisdiction of the courts of the Afar National Regional State on the basis of the constitution of the Regional State;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 47 (2.2) of the constitution of the Afar National Regional State, it is hereby proclaimed as follows:

PART ONE
General

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as "the Afar National Regional State Courts Establishing Proclamation No. 3, 1998.

2. *Definitions*
In this Proclamation:
1. "Regional State/Government" means the Afar National Regional State.
2. "Officials of the Regional State" means members of the Council of the Regional State: regional bureau heads, judges of the region's supreme court and other officials of the regional state of equivalent rank;
3. "Court" means a regional supreme court, high court or woreda court established by this proclamatioin.

፬· "በሥራ ላይ ያሉ ሕጎች" ማለት የፌዴራሉንና የክልሉን ሕገ መንግሥት የማይቃረኑ የክልሉን መንግሥት ሥልጣን የሚመለከቱ ነባር ሕጎች ሲሆኑ፡ ወንጀለኛ መቅጫና ፍትሐ ብሔር ሕጎችን፡ የወንጀለኛ መቅጫ እና የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕጎችን እንዲሁም ሌሎች ሕጎችን ይጨምራል።

፭· "ሰው ማለት" የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነትመብት የተሰጠው አካል ነው።

፫· መቋቋም

ከዚህ የሚከተሉት የክልሉ መንግሥት ፍርድ ቤቶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል።

፩· ጠቅላይ ፍርድ ቤት

፪· ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና

፫· ወረዳ ፍርድ ቤት

፬· የፍርድ ቤቶች ዓላማ

የክልሉ መንግሥት ፍርድ ቤቶች የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩዋቸዋል።

፩· በፌዴራሉና በክልሉ ሕገ መንግሥት የተረጋገጡትን የግለሰብ መብቶች ነፃነቶችና ጥቅሞች ማስከበር፣

፪· በፌዴራሉና በክልሉ ሕገመንግሥት የተረጋገጡትን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሥርዓትን ማስከበር፣

፫· ሕግና ሥርዓት ተጠብቆ ፍትሕና ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ።

ክፍል ሁለት
ስለፍርድ ቤቶች የወል የዳኝነት ሥልጣን

፭· መሠረት፡

የክልል ፍርድ ቤቶች በፌዴራሉና በክልል መንግሥት፡ ሕገ መንግሥት ለክልሉ መንግሥት ተለይተው በተሰጡ የሥልጣን ክልል በሚወድቁ ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል።

፮· የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተለይተው ከተሰጡ የወንጀል ጉዳዮች በስተቀር የክልል ፍ/ቤቶች በሥራ ላይ ባሉት የወንጀል ሕጎች ውስጥ በተደነገጉት ወንጀሎች ላይ የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል።

፯· የፍትሐብሔር የዳኝነት ሥልጣን

በፌዴራልፍርድ ቤቶች አዋጅ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተለይተው ከተሰጡት የፍትሐብሔር ጉዳዮች በስተቀር የክልል ፍርድ ቤቶች በሌሎች የፍትሐብሔር ክርክሮች ላይ የፍትሐብሔር የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል።

፰· የክልል ፍርድ ቤቶች ስለሚሠሩባቸው የፍሬ ነገር ሕጎች

፩· የክልል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክልላቸውን መሠረት አድርገው የሚቀርቡላቸውን ጉዳዮች ወይም ክርክሮች በክልሉ ሕገ መንግሥት በክልሉ ሕጎች እና ከዚህ አዋጅ ጋር በማይቃረኑ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች መሠረት ይዳኛሉ።

፪· የክልል ፍ/ቤቶች የያዙት ጉዳይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ካስነሳ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት ለክልሉ ሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ መላክ ይኖርባቸዋል።

፱· የክልል ፍ/ቤቶች ስለሚሠሩባቸው የሥነ ሥርዓት ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የማይጋጩ በሥራ ላይ ያሉ የወንጀለኛና የፍትሐብሔር ሥርሥርዓት ሕጎች እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

4. ''Laws in force'' means all previous laws in force which are not inconsistent with the Federal and the Regional state's Constitution and the powers of the Regional State including civil and penal codes, civil and penal code procedures and other laws.
5. ''Person'' means any human person or a body having a legal personality.

3. *Establishment*

The following courts of the Regional State have been established in accordance with this proclamation:

1. A Supreme Court
2. A High Court and
3. A Woreda Court

4. *Court Objectives:*

The Regional State's courts shall have the following aims and objectives:

1. to ensure respect for the freedoms, rights and interests of individuals as provided for in the federal and regional state constitutions;
2. to uphold the political, economic and social systems established in accordance with the federal and regional state constitutions;
3. to ensure that peace and justice are maintained in accordance with the law.

PART TWO
Common Jurisdiction of Courts

5. *Principle*

Regional courts shall have jurisdiction over cases as specified by the constitutions of the Federal and Regional State and passed to the jurisdiction of the Regional State.

6. Regional Courts shall have jurisdiction over cirminal cases cited in criminal laws in force except those that have been specified and given to the federal courts by the Proclamation of the Federal courts.

7. *Civil Jurisdiction*

Regional couts shall have jurisdiction over all civil cases in the region except those that have been specified by the Proclamation of the Federal Courts and given to the federal courts.

8. *Substantive Laws to be Applied by Courts of the Regional State*

1. The Regional State Courts shall settle cases or disputes submitted to them within their jurisdiction on the basis of the regional constitution, regional laws and other laws in force where these are not inconsistent with this proclamation.
2. Where a case brought before them gives rise to issues of constitutional interpretation, the Courts of the Regional State shall refer the case to the Regioinal Council of Constitutional Inquiry prior to givin decision on the matter.

9. Procedural Laws to be Applied by Regional State Courts

The Criminal and Civil Procedure Codes as well as other relevant laws in force shall apply with respect to matters no provided or under this Proclamation insofar as they are not inconsistent therewith.

ክፍል ሦስት

የክልሉ ጠቅላይ ፍ ቤት የዳኝነት ሥልጣን

፲· የክልሉ ጠቅላይ ፍ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን

የክልሉ ጠቅላይ ፍ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ብቸኛ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።

፩· የክልሉ መንግሥት ባለሥልጣኖች በሥራ ኃላፊነታቸው ምክንያት ተጠያቂ በሚሆኑባቸው የወንጀል ጉዳዮች፡

፪· በሕግ መሠረት ከአንድ የክልል ከፍተኛ ፍ ቤት ወደ ሌላ የክልል ከፍተኛ ፍ ቤት ወይም ወደራሱ እንዲዛወር በሚቀርብ ጥያቄ ላይ፡

፫· በፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን የሚቀርቡ ጉዳዮችን።

፲፩· የክልል ጠቅላይ ፍ ቤት የይግባኝ ሥልጣን

የክልሉ ጠቅላይ ፍ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።

፩· ከከፍተኛ ፍ ቤቶች በሕግ መሠረት በይግባኝ የሚቀርቡለትን ጉዳዮች፡

፪· ከፍተኛ ፍ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት በሚሰጠው ውሣኔ ላይ የሚቀርቡ ይግባኝ።

፲፪· የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥልጣን

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ ቤት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ጉዳይ በሰበር የማየት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ጠቅላይ ፍ ቤት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን የሚከተሉትን የክልል ጉዳዮች በሰበር የማየት ሥልጣን ይኖረዋል።

፩· የክልል ከፍተኛ ፍ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች፡

፪· የክልል ጠ ፍ ቤት መደበኛ ችሎት የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች።

ክፍል አራት

ስለ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የወረዳ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን

፲፫· የክልል ከፍተኛ ፍ ቤት የዳኝነት ሥልጣን

የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።

፩· በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በፍትሐብሔርና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ወይም በሌሎች ሕጎች ለከፍተኛ ፍ/ቤት ተብሎ በተወሰነው መሠረት የሚቀርቡ ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ የመወሰን፡

፪· በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሥልጣኑ የሚቀርቡለትን ጉዳዮች አይቶ የመወሰን፡

፫· ከወረዳ ፍርድ ቤቶች በይግባኝ የሚቀርቡለትን ጉዳዮች አይቶ የመወሰን፡

፬· በሕግ መሠረት አንድን ጉዳይ ከአንድ የወረዳ ፍ/ቤት ወደ ሌላ ወረዳ ፍ/ቤት ወይም ወደራሱ እንዲዛወር በሚቀርብ ጥያቄ ላይ፡

፭· በሕግ ሥልጣን በተሰጣቸው የዳኝነት ሰጪ አካላት በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡለትን ይግባኝ አይቶ የመወሰን።

፲፬· የክልል ወረዳ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን

የክልል ወረዳ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።

፩· በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔርና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕጎች ወይም በሌሎች ሕጎች ለወረዳና ለአውራጃ ፍርድ ቤቶች በተሰጡ ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ ክርክሮችን አይቶ የመወሰን ፡

፪· በማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ይግባኞችን አይቶ የመወሰን ።

PART THREE

Jurisdiction of the Regional Supreme Court

10. *First Instance Jurisdiction of the REgional Supreme Court*

The Regional Supreme Court shall have exclusive first instance jurisdiction over the following:

1. Offenses for which officials of the Regional State are held liable in connection with their official responsibility;
2. Application for change of venue from one Regional High Court to anothr or to itself, in accordance with the law; and
3. Cases referred to under orders of the Federal High Court.

11. *Appelate Jurisdiction of Regional Supreme Court*

The Regional Supreme Court shall have hurisdiction over:

1. appelate cases submitted in accordance with the law from high courts; and
2. appelae-case involving a decision of a high court made in accordance with the federal first instance jurisdiction.

12. *Power of Cassation of the Regional Supreme Court*

Without prejudice to the Federal supreme Courts' power of cassation over cases containing fundamental error, the Regional Supreme Court shall have the powr of cassation over the following cases which contain fundamental error:

1. final decisions of the Regional High Court rendered in its appelatd jurisdiction; and
2. final decisions rendered at the regular diivision of the Regional Supreme Court.

PART FOUR

Jurisdiction of the Regional High Court and Woreda Court

13. *Jurisdiction of the Regional High Court*

The Regional High Court shall have Jurisdiction over the follwing cases:

1. Without prejudice to the jurisdiction of the Federal Supreme Court as specified in the Proclamation of Federal Courts, cases requiring first instance jurisdiction directed to it in accordance with civil and cirminal code procedures;
2. Cases directed to it by the Federal First Instance Court.
3. Cases directed to it by woreda courts for appelate jurisdiction;
4. Cases related to issues requiring submission, according to law, from one woreda court to another or to itself; and
5. Cases requiring appelate jurisdiction as directed to it by legally authorized judicial organs.

14. *Jurisdiction of the Regional Worda Court*

The Regional Woreda Court shall have juridsdiction over the following cases:

1. without prejudice to the jurisdictionof the Federal First Instance Court as specified in the Proclamation of Federal Court, cases directed to Woreda and Awraja Courts in accorodance with civil and criminal court procedures and other laws; and
2. cases directed to it for appelate jurisdiction following decisions by social courts.

ክፍል አምስት
ስለፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች

፲፭· የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

፩· የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሕግ መሠረት የክልሉን ፍርድ ቤቶች ለማስተዳደር ኃላፊ ይሆናል ።

፪· ይህ አጠቃልይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሬዚዳንቱ፤

ሀ) ከክልል ከፍተኛና ወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች ጋር በመመካከር የክልል ዳኞችን ይደለድላል ፣ ሥራ ይሰጣል ፣ ያስተዳድራል ፣

ለ) ለክልል ፍርድ ቤቶች አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ከከፍተኛና ከወረዳ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች ጋር በመመካከር ይቀጥራል ፣ ያስተዳድራል ፣

ሐ) የክልሉን ፍርድ ቤቶች ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል ፣ ሲፀድቅም ሥራ ላይ ያውላል ፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን በውክልና ለሚሰሩ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የበጀት ማካካሻ ጥያቄ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀርባል ፣ ተከታትሎ ያስፈፅማል ።

መ) የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕግ መጽሔት እንዲዘጋጅ ያደርጋል ፣

ሠ) ስለክልል ፍርድ ቤቶች ሥራ በስታትስቲክስ የተደገፈ መግለጫ እንዲዘጋጅ ያደርጋል ፣ የከፍተኛና የወረዳ ፍርድ ቤቶችም ተመሳሳይ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ያደርጋል ።

ረ) የዳኞችና የሌሎች ሠራተኞች ትምህርትና ሥልጠና የሚካሄድበት ሁኔታ ያመቻቻል ፣

ሰ) ስለክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራ አካሄድ ለክልሉ ምክር ቤት ጥናታዊ ዘገባዎችን ያቀርባል ፣

ሸ) የተከላካይ ጠበቆችን ቢሮ ያደራጃል ፣

ቀ) በሕግ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ፣

፫· የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባሩን በውክልና ሊሰጥ ይችላል ።

፲፮· የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት

የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ፣

፩· በፕሬዚዳንቱ የሚመራለትን ሥራ ያከናውናል ፣

፪· ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ ፕሬዚዳንቱን ተክቶ ይሠራል።

፲፯· ስለክልል ከፍተኛና ወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች ሥልጣንና ተግባራት

የፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንት

፩· ፍርድ ቤቱን ይወክላል፣

፪· የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የፍርድ ቤቱን ሠራተኞች ያስተዳድራል ፣

፫· ስለፍርድ ቤቱ ሥራ በስታትስቲክ የተደገፈ መግለጫ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣

፬· የፍርድ ቤቱን ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ያቀርባል ፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል ፣

፭· ትምህርታዊ የሆኑ የየዓመቱ ፍርዶችና ውሳኔዎች ተመርጠው ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት እንዲላኩ ያደርጋል ፣

፮· ስለሥራው እንቅስቃሴ በየጊዜው ለክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ሪፖርት ያቀርባል ፣

፯· በሕግ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ።

PART FIVE
The Presidents of the Courts

15. *Powers and Duties of the Presidnet of the Regional Supreme Court*

1. The President of the Regioinal Supreme Court shall be responsible for the administration of the Regional Courts in accordance with the law.
2. Without Prejudice to the generality of sub-article (1) hereof, the president of the Regional Supreme Court shall:
   (a) In consultation with the Presidents of the Regional High Court and Woreda Court, place, assign and administer regional judges;
   (b) In consultatioin with the Presidents of the Regional High Court and Woreda Court, employ and administer personnel necessary for Regional High Courts;
   (c) Prepare and submit to the Region's House of the People the work plan and budget of Regional Hight Courts and implement same upon approval, and submit to the FederalSupreme Court requests by the regional courts for budgetary subsidy and folows its execution;
   (d) Cause the publication of the law journal of the Regional Supreme Court.
   (e) Cause the preparation of statements concerning the activities of regional courts and the submission of similar reports by high courts and woreda courts, as supported by statistical data;
   (f) Fcilitate conditions for the education and training of judges and other personnel;
   (g) Submit, to the Regional House of the People, researched reports on the judicial activities of Regional courts;
   (h) Organize the public defense office;
   (i) Perform such other duties as may be entrusted to him by law.
3. The President of the Regional Supreme Court may, whenever necessary, delegate his powers and duties listed herewith to another.

16. *Vice-President of the Regional Supreme Court*

The Vice-President of the Regional Supreme Court shall:
1. discharge duitics to be assigned to him by the President;
2. serve in the President's stead, while the President is absent

17. *Powers and Duties of the Presidents of the Regional High Court and Woreda Court*

The President of each Court shall;
1. Represent the court;
2. Administer personnel of the Court subject to directives to be given by the President of the Regional Supreme Court,
3. Cause the preparation of statements, supported by statistical data, regarding the activities of the court;
4. Prepare and sumbit to the President of the Regional Supreme court the work plan and budget of the Court and implement same upon approval;
5. Cause the selection, and sumbission to the President of the Regional Supreme Court, of instructive judgments and decisions of the year;
6. Submit to the President of the Regional Supreme Court periodic reports on the activities of the Court; and
7. Perform such other duties as may be entrusted to him by law.

ክፍል ስድስት

ስለክልል ፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና የዳኝነት ሥራ አካሄድ

፲፰. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችና ሌሎች ሠራተኞች

፩. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አንድ ፕሬዚዳንት ፣ አንድ ምክትል ፕሬዚዳንት እንዲሁም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞች ይኖሩታል፡

፪. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለሥራው የሚያስፈልጉ ሠራተኞች ይኖሩታል ።

፲፱. ስለፍርድ ቤት ችሎቶች

፩. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፡ ከፍተኛ ፍ/ቤትና ወረዳ ፍ/ቤቶች የሚከተሉት ችሎቶች ይኖሩታል ።

ሀ) የፍትሐብሔር ችሎት ፡

ለ) የወንጀል ችሎት ፡ እና

ሐ) እንደአስፈላጊነቱ የሥራ ክርክር ችሎት።

፪. በጠቅላይ ፍ/ቤት እና በከፍተኛ ፍ/ቤት በእያንዳንዱ ችሎት አንድ ሰብሳቢና ሁለት ዳኞች ሆነው ያስችላሉ ።

፫. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንቶች ወይም ምክትል ፕሬዚዳንቶች በማናቸውም ችሎት ሰብሳቢ ሆነው ሊሰሩ ይችላሉ።

፬. በእያንዳንዱ የወረዳ ችሎት አንድ ዳኛ ሆኖ ያስችላል ፣ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ ድምፅ የመስጠት መብት ሳይኖራቸው ሁለት ከሕዝብ የተመረጡ ተቺዎች ሊኖሩ ይችላሉ።

፳. ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ስለሚሰየሙበት ችሎት

፩. የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት በራሱ አነሳሽነት ወይም በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎት አሳሳቢነት ወይም ከተከራካሪ ወገኖች በአንዱ ጥያቄ ሲቀርብለት አንድን ጉዳይ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመው እንዲያዩት ለማድረግ ይችላሉ ።

፪. ይህ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ጉዳዮች የሚታዩት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት ነው ።

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲(፩) እና (፪) የተጠቀሱት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ የሚያያቸው ጉዳዮች፡

ለ) በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች መካከል መሠረታዊ የሆነ የትርጉም ልዩነት የተፈጠረበትን ሕግ የሚመለከቱ ጉዳዮች ሲኖሩ ፣

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ የተጠቀሱት ጉዳዮች በሰበር እንዲሰሙ ሲወሰን ።

፳፩. ስለማስቻያ ሥፍራ

፩. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የማስቻያ ሥፍራ በክልሉ መንግሥት ርዕሰ ከተማ ይሆናል ፣

፪. የክልሉ ከፍተኛና ወረዳ ፍርድ ቤቶች የማስቻያ ሥፍራ በሚገኙበት የዞንና የወረዳ ዋና ከተሞች ይሆናል ፣

፫. በየትኛውም እርከን ላይ የሚገኝ የክልል ፍ/ቤት ቀልጣፋ ፍትሕ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማንኛውም ሥፍራ ተዘዋውሮ ሊያስችል ይችላል ።

፳፪. በግልጽ ችሎት ስለማስቻል

፩. የክልል ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ያስችላሉ።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም ፣ ለዳኝነት አሠራር አግባብነት ያላቸው የሥነሥርዓት ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በዝግ ችሎት ያስችላሉ ።

PART SIX

Regional Court Structure and the Administration of Justice

18. *Judges and Other Personnel of the regional Supreme Court*
   1. The Regional Supreme Court shall have a President, a vice-President and the necessary judges.
   2. The Regional Supreme Court shall have the personnel necessary for its function.

19. *Divisions of the Courts*
   1. The Regional Supreme Court, High Court and Woreda Courts shall have the following divisions:
      (a) a Civil Division
      (b) a Criminal Division; and
      (c) a Labour Division, as necessary.
   2. There shall sit a presiding judge and two other judges in each division of the Regional Supreme Court and a High Court.
   3. The Presidents of the Regional Supreme Court And High Court, or their vice-presidents, may preside over any division.
   4. There shall sit only one judge at a division of a woreda court; however, two publicly elected persons, who may not have a decisive voice, may sit as commentators.

20. *Division with not less than five judges:*
   1. The President of the Regional Supreme Court may on his own initiative or suggestion by a division of the Regional Supreme Court or one of the parties so petitions, direct a case to be heard by a division withnot less than five judges sitting.
   2. With out prejudice to the generality of the above statement, the following cases shall be heard by a division with not less than five judges sitting:
      (a) cases falling under the first instance jurisdiction of the Supreme Court as provided for in Article 10 sub-articles 1 and 2 of this Proclamation;
      (b) cases relating to a provision of law having caused a fundamental difference in interpretation amongst divisions of the Regional Supreme Court; and
      (c) cases referred to under Article 12 of this Proclamation, where it is decided that they be heard in cassation.

21. *Place of Sittings*
   1. The Regional Supreme Court shall sit in the capital of the Regional State.
   2. The Regional High Court and Woreda Courts shall sit in the capitals of the respective zones and woredas.
   3. A Regional Court of any level may, where it finds it necessary for the efficient rendering of justice, hold circuit hearings in any place designated for its jurisdiction.

22. *Open Hearing*
   1. Regional courts shall hear cases in open
   2. Not withstanding the provisions of sub-Article (1) hereof and without prejudice to procedural laws relevant to adjudication, cases may be heard in camera in consideration of the following: